# ትንሣኤ መጽሔት

የ፲፱፻፸፪ ዓ.ም. የቀን መቁጠሪያ ።

## መስከረም

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ማ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ረ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ኀ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ዓ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ቅ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| እ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |

## ጥቅምት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ |
| ማ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ረ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ኀ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ዓ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ቅ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| እ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |

## ኅዳር

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ማ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ረ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ኀ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| ዓ | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |
| ቅ | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ | |
| እ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |

## ታኅሣሥ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ማ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ረ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ኀ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ዓ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ቅ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| እ | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |

## ጥር

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ማ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ረ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ኀ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ዓ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ቅ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| እ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |

## የካቲት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ |
| ማ | | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ |
| ረ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ኀ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ዓ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ቅ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| እ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |

## መጋቢት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ማ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ረ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ኀ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ዓ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| ቅ | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |
| እ | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ | |

## ሚያዝያ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ማ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ረ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ኀ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ዓ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ቅ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| እ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |

## ግንቦት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ |
| ማ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ረ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ኀ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ዓ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ቅ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| እ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |

## ሰኔ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ማ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ረ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ኀ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| ዓ | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |
| ቅ | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ | |
| እ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |

## ሐምሌ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ማ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ረ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ኀ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| ዓ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |
| ቅ | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ | |
| እ | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ | |

## ነሐሴ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ | | ፭ | ፲፪ | ፲፱ | ፳፮ |
| ማ | | ፮ | ፲፫ | ፳ | ፳፯ |
| ረ | | ፯ | ፲፬ | ፳፩ | ፳፰ |
| ኀ | ፩ | ፰ | ፲፭ | ፳፪ | ፳፱ |
| ዓ | ፪ | ፱ | ፲፮ | ፳፫ | ፴ |
| ቅ | ፫ | ፲ | ፲፯ | ፳፬ | |
| እ | ፬ | ፲፩ | ፲፰ | ፳፭ | |

## ጳጉሜን

| ቅ | እ | ሰ | ማ | ረ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ |

# ትን



እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ አሸጋገረዎ ።










www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጕምር እንዲተረ ጕሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| እንኳን አደረሳችሁ | ፩ |
| ደብዳቤዎች | ፪ |
| ሰላም ለዓለም | ፫ |
| ይህን ያውቁ ኖሯል ? | ፬ |
| ክርስቲያናዊ ሕይወት | ፭ |
| የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች | ፮ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፱ |
| ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች | ፲፪ |
| የወጣቶች ዓምድ | ፲፬ |
| እምነት ስትመዘን | ፲፮ |
| የሃይማኖት ዓምድ | ፲፰ |
| ሊቃውንቶቻችን | ፲፱ |
| የጤና ዓምድ | ፳፩ |
| ዜና ሀገረ ስብከት | ፳፫ |
| የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና | ፳፭ |
| የሴቶች ዓምድ | ፳፮ |
| አዛውንቶቻችን | ፳፯ |
| የመስቀሉ ቃል | ፳፰ |


# እንኳን ለአዲሱ ዓመት ሺህ ዘጠኝ መቶ

## ሰባ ሁለት ዓመተ ምሕረት እግዚአብሔር አደረሳችሁ !

## ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሁለት ዓመተ ምሕረት

የሰላምና የጤና ፤

የፍቅርና የደስታ ፤

የነፃነትና የእኩልነት ፤
የፍትሕና የርትዕ ፤

የዕውቀትና የንቃት ፤

የምርትና የብልጽግና ፤

የኃይልና የድል ፤

የማነጽና የመገንባት ዓመት ይሁንላችሁ ፤

በማለት የትንሣኤ መጽሔት ለአንባቢዎቹ ሁሉ መልካም ምኞቱን ይገልጣል ።

ከዚህም ጋር ትንሣኤ የሚከተለውን መንፈሳዊ ምክሩን ለአንባቢዎቹ ይለግሳል ፤

በአዲሱ ዓመት በአዲስ መንፈስና

ኃይል ተነሡ ፤

ለሥራ ታጠቁ ፤

ሁሉን ተማሩ ፤

ሁሉን አስተምሩ ፤

ሁሉን መርምሩ ፤

ነገር ግን መልካሙን ነገር ያዙ ፤

ንቁ ፤ ቁሙ ፤

በእግዚአብሔር እመኑ ፤

በእምነታችሁ ጽኑ ፤

ለመጭውም ዓመት እግዚአብሔር

በሰላም ያድርሳችሁ ።

ትንሣኤ መጽሔት

ቁጥር ፳፬ ፲፱፻፹፪ ዓ. ም.

### ያ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. የአጽዋማትና የበዓላት ማ ው ጫ

| | |
|---|---|
| አበቅቴ | ፲፬ |
| መጥቅዕ | ፲፮ |
| ነነዌ ጥር | ፲፱ |
| በዓተ ጾም የካቲት | ፫ |
| ደብረ ዘይት የካቲት | ፴ |
| ሆሣዕና መጋቢት | ፳፩ |
| ስቅለት መጋቢት | ፳፮ |
| ትንሣኤ መጋቢት | ፳፰ |
| ርክበ ካህናት ሚያዝያ | ፳፪ |
| ዕርገት ግንቦት | ፯ |
| ጰራቅሊጦስ ግንቦት | ፲፯ |
| ጾመ ሐዋርያት ግንቦት | ፲፰ |
| ጾመ ድኅነት ግንቦት (ረቡዕና ዓርብ) | ፳ |




www.ethiopianorthodox.org

## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ ፤
አዲስ አበባ ።

፩ኛ/ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለይ በደብረ ሊባኖስ ገዳም አንድ ቄስ ወይም ዲያቆን ካልመነኮሰ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለመቀደስ ፤ አይችልም ፤ በዚህ ምክንያት የተነሣ ብዙ ካህናትና ዲያቆናት ቅዳሴ እየቀደሱ የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ስለሚገደዱ በልጅነታቸው እየመነኮሱ ሲቀድሱ ከቆዩ በኋላ ትምህርታቸውን አሻሽለው ወይም በልዩ ልዩ ሙያ ሠልጥነው ወደከተማ ገብተው ሥራ በሚይዙበት ጊዜ ቆባቸውን አውልቀው በመጣል ሚስት አግብተው ትዳር በመመሥረት ልጅ ይወልዳሉ ። አባ እየተባሉ ሲጠሩ የነበሩትም አቶ ይባላሉ ።

ስለዚህ ይህ ከመሆኑ በፊት ፤

ሀ/ ምንኩስና ወይም ቆብ የእግዚአብሔር አክሊል እንደመሆኑ መጠን እንደገበያ ልብስ ለጠየቀው ሁሉ ከመስጠቱ በፊት ጠያቂው ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበትና የዕድሜ ገደቡም የሚፈቅድለት መሆኑን ለምን አናጠናም ?

ለ/የምንኩስና ማዕርግ ለአንድ ሰው ሊሰጥ የሚችለው የዕድሜ ገደቡ ከስንት እስከ ስንት ድረስ ሲሆን ነው ።

ሐ/ ካህን ወይም ዲያቆን ካልመነኮሰ በገዳማት ቤተ መቅደስ ውስጥ ገብቶ ለመቀደስ አይችልም የሚለውን ሕግስ ለምን እንዲሻሻል አይደረግም ?

ማሳሰቢያ ፡—ጥያቄውና መልሱ በመጽሔትና በጋዜጣ እንዲወጣልኝ እጠይቃለሁ ።

«ኢትዮጵያ ትቅደም»
ከተስፋዬ ኢሳይያስ ንግድና ቱሪዝም ሚኒስቴር የስልክ ቁ/ 44 82 00
አዲስ አበባ

● ት/ መጽሔት ፤ ለዚህ ጥያቄ ማንኛውም ሰው ወይም የሚመለከተው ክፍል መልስ ቢሰጥበት የተሻለ ስለመሰለን ጥያቄዎን አውጥተነዋል ።

✶ ✶ ✶

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ጸጋ ይብዛላችሁ ። የጌታ መንፈስ ከእናንተ ጋር ሆኖ ለጥያቄዬ መልስ እንደምትሰጡኝ አምናለሁ ።

ሐዋርያው ዮሐንስ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ ያሉትን የመከራ ጊዜዎችን በምሳሌ ሲናገር አርባ ሁለት ወር ቅድስት ከተማ በአሕዛብ ትረገጣለች ። ሁለቱ ምስክሮች ማቅ ለብሰው ፩ሺ፪፻፷ ቀናት ትንቢት ይናገራሉ ራእ ፲፩.፪—፫(ሴቲቱም ፩ሺ፪፻፷ ቀናት ከእባቡ ፊት ርቃ ወደ በረኃ ትሸሻለች ) (ራእ.፲፪. ፮ እና ቁ. ፲፬ ) እዚህ ላይ ያልገባኝ ፩ኛበቁጥር የተጠቀሱ ጊዜያቶች ሌላ ትርጉም አላቸውን ? ካላቸው ያብራሩልኝ ።

፪ኛ ሴትዮዋ ማን ናት ፤ በቁጥር የተጠቀሰው ዘመን ስንት ዓመት ነው ፤

፫ኛ ራእ ፲፫ ፡ ፲፮—፲፰ የአውሬው ስም ወይም የስሙ ቁጥር ምልክት ፮፻፷፮ ምሥጢር ምንድን ነው ?

አብድያ ዐብየ
ከአ-አ

● አብድያ ዐብየ ጥያቄዎ የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥጢር ለመረዳት ስለሆነ አስደስቶናልና መልሱን እንደሚከተለው እንሞክራለን ።

፩ኛ/ሀ/፩ሺ፪፻፷ ሦስት ዓመት ተኩል ይሆናል ፤

ለ/ ፵፪ ወራት ሦስት ዓመት ተኩል ይሆናል ፤

ሐ/ አንድ ዘመን ዘመናትም የዘመን እኩሌታ ሦስት ዓመት ተኩል ይሆናል ። ይህ ቁጥር በአይሁድ ዘንድ ነጥብ ያለው ቁጥር ነው ። አንጥያኮስ ቅድመ ክርስትና በ፩፻፷፰ ዓ/ ዓለም የአይሁድን ቤተ መቅደስ ካረከሰ ከ፫ ዓመት ተኩል በኋላ የቤተ መቅደስ ማንጻት ሆኗል ። ሦስት ዓመት ተኩል በሙሉ የመከራ ዓመታት ነበሩ ። ከዚህ በኋላ ዳንኤልም በዚህ ቁጥር ተጠቅሞአል ።
(ዳን ፯ ፡ ፳፭ ። ፲፪ ፡ ፯)

፪ኛ/ ሴትዮዋ ፤
ሀ/ቤተ እስራኤል ናት ፫ ዓመት ተኩል በአንጥያኮስ መከራ ተቀብላለችና
ለ/ ቤተ ክርስቲያን ናት ፤
ሐ/ እመቤታችን ናት ፫ ዓመት ተኩል በስደት ኖራለችና

፫ኛ/ ፮፻፷፮ የሰው ቁጥር ነው በተባለው መሠረት ክርስቲያኖች እንደሚከተለው ተርጉመዋል ። አቆጣጠሩ ሀ/ በግሪክ ፤ለ/በዕብራይስጥ ሐ/በላቲን ፊደላት አቆጣጠር ነው ። ለምሳሌ የክርስቲያኖች ጠላት የነበረውን የኔሮንን ስም በላቲን ፊደል እንቊጠር ። ኔ- ፶ ኢ-፮ አር -፭፻ ኦ-፷ን ፶ ድምር ፮፻፷፮ ይሆናል ። በዕብራይስጥም ቄሳር ኔርዎን ብለን እንቊጠር ቄ- ፩፻ሳ ፷ ር ፪፻ ኔ ፶ ር-፪፻ ዎ ፮ን ፶ ድምር ፮፻፷፮ ይሆናል።
አሁንም ሌላ ሐሳብ እንፈልግ ።

«አርኖዩም እኔ እክዳለሁ ማለት ነው» ቃሉም ግሪክ ነው ። ኤ ፩ አር ፩፻ ነ ፶ አ ፸ ዩ ፬፻ ኤም ፵ ኢ፰ ድምር ፮፻፷፮ ይሆናል ። ቁጥሩ በዚህ ዓይነት ፍጻሜ አልባ ነው ። የብዙ ሰዎችንና ነገሮችን ስም ብንመረምር ተመሳሳይ ቁጥር እናገኛለን ።

✶ ✶ ✶

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ ፤
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ ሰላምታየን አቀርባለሁ አንዲት ልጅ ወድጃለሁ እር

ወደ ገጽ ፲ ዞሯል



ርእሰ አንቀጽ

# ሰላም ለዓለም

ዓለም በ፳ኛው ምእት ዓመት በጥበብ የተራቀቀውን ያህል ስለሰላም ቢያስብ በአንደኛው ፤ በሁለተኛውና በሦስተኛው ዓለማት የኑሮና የርዕዮተ ዓለም መለያየት እንደማይኖር ብዙዎች ይገምታሉ ። ምክንያቱም ሰላም ካለ ሦስተኛው ከሁለተኛው ሁለተኛውም ከአንደኛው ዓለም ጋር በሰላም ተወያይቶ ሰፊ የሆነውን መለያየት ያስወግድ ነበር ። ዳሩግን ሰላም በዓለም አይታይም ። ዓለም በቀን ፤ በወርና በዓመት ከሚያመርታቸው መሣሪያዎች ብዙዎቹ ፀረ ሰላም ናቸው ። ዓለም በየቀኑከሚያስተላልፋቸው ዜናዎች የሰውን ልብ የሚያሸብሩ የመዓትና የመቅሠፍት ዜናዎች ይሰማሉ ። እርግጥ በአንዳንድ አህጉር ሰላም እንዳለ ይነገራል ። ሆኖም ያ ነገር በትክክል ሲታይ ፀጥታ እንጂ ሰላም አይደለም ። ዝምታ እንጂ ሰላም አይደለም ። ታዲያ ዝምታ እኮ ሰላምን አያመለክትም ። ሰላም ማለት እኩልነት ፤ ነፃነት ፤ መብትና ትክክለኛ ፍትሕያሉበት ነገር ነው ።

ስለዚህ አዲሱ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሁለት ዓመተ ምሕረት ለዓለም ሁሉ የሰላም ዓመት እንዲሆን የዓለም ሕዝብ ስለሰላም እንዲያስብ ያስፈልጋል ። በአለፈው ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አንድ ዓመተ ምሕረት የታላላቅ አህጉር መሪዎች ስለሰላም ተወያይተዋል ። ስለጦር መሣሪያ ቅነሳም ተስማምተዋል ። የሃይማኖት መሪዎችም ሁሉ ስለሰላም ጸሎት አድርገዋል ። ጦርነትንም ተቃውመዋል ። አዎ ይህ ሁሉ በአዲሱ ዓመት በተግባር ላይ ውሎ ሰላም ይሠፍን ዘንድ ዓለም ተስፋ ያደርጋል ። ነገር ግን ሰላም ከማን ይጠበቃል ? ሰላምን ለዓለም ሊሰጥ የሚችል የሰላም ባለቤት ማን ነው ? ምንጊዜም ቢሆን ሰላም ከዓለም የሚጠበቅ አይመስልም ። ሰላምን ለዓለም ሊሰጥ የሚችል ራሱ ዓለም አይደለም ። ምክንያቱም የበለጸጉ አገሮች የኢኮኖሚያቸው እድገት በጦር መሣሪያ ምርታቸው ስለሆነ መሪዎቻቸው ሰላምን አይሹም ።

ሰላም በዓለም ውስጥ የሚገኝ ቢሆን ኖሮ የዓለም ሕዝቦች እስካሁን እንደ አንድ ቤተሰብ በሆኑ ነበር ። ከመጠን በላይ የሆነ ልዩነት ሳይኖር መጠነኛ እኩልነት ይኖር ነበር ። በደቡብ አፍሪካ በጥቂት ዘረኞችከተማ በራፍ ላይ «ጥቁር ሰውና ውሻ አይገቡም ፤ ርካሽ ሥራ ለርካሽ ሰው» እየተባለ የሚለጠፈው ማስታወቂያ በተሠረዘ ነበር ። ዳሩ ግን የጥሉን ግድግዳ አፍርሶ ሰላምን ፤ አድልዩነትን ደምስሶ አንድነትንና እኩልነትን ፤ የባርነትን ቀንበር ሰብሮ ነፃነትንና ዘረኛነትን ፤ አድልዎን አጥፍቶ ርቱዕ ፍትሕን ሊመሠርት የሚችል በዓለም ላይ ባለመኖሩ ዓለም የጥላቻ አውድማ ሆና ትታያለች ። እንግዲህ ሰላም ከማን በማን ይገኝ ይሆን ? ።

አዎ ሰላም ከእግዚአብሔር ነው ። ሰላም በእግዚአብሔር ነው ። የሰላም ባለቤት እርሱ ብቻ ነውና ። ስለዚህ በአዲሱ ዓመት ዓለም የሰላም ቦታ እንዲሆን የዓለም ሕዝብ ሁሉ እግዚአብሔርን ማወቅ ፤ ስለሰላም እግዚአብሔርን መጠየቅ ያስፈልገዋል ። እግዚአብሔር የሚሰጠው ሰላም ዓለም ከሚሰጠው ሰላም ልዩ ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖረዋል ?

በእጅጉ ረታ ።

ጾም ከተለዩ የምግብ ዓይነቶች ለተለዩ ወቅቶች መወሰን መሆኑን እናውቃለን ። ይህ ሳይቀር ወይም የሚመረጥ ነገር ሳይኖር ፤ ሳጭር ወይም ለረዥም ጊዜ ከማናቸውም ምግብ በገዛ ፈቃድ መከልከል የጾም አንዱ ክፍል መሆኑ አዲስ ነገር አይደለም ። በግልም ሆነ በማኅበር መጾም ከጥንት ጀምሮ በሕዝብም ሆነ በአሕዛብ የተለመደ ነበር ። የጾሙ ሥርዓት ፤ የአፈጻጸሙም ሁናቴ የተለያየ ቢሆንም ፤ በሃይማኖቶቹ ሁሉ ጾም የተቀደሰ ሥፍራ የተሰጠው መሆኑን በ፳፫ ቁጥር ትንሣኤ መጽሔት ማቅረቤ ይታወሳል ። ታዲያ ጾም በክርስትና እምነት ውስጥ ያለው ሥፍራ ምንድነው፣ ለምንስ እንጾማለን ? እነዚህን ጥያቄዎች በቀጥታ ከመመለሳችን በፊት እንደ ማናቸውም የአምልኮ ሥርዓታችን ሁሉ የምንጾመውም የጾም ሥርዓት ከሞላ ጐደል ከአይሁድ ጾም ሥርዓት ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ በቅድሚያ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለዚሁ ጉዳይ የተጻፉትን ማወቁ ሳይጠቅም አይቀርም ።

በሕዝበ — አይሁድ ዘንድ ጾም መቼ እንደተጀመረ በትክክል የሚታወቅ አይመስልም ። ገና የኦሪት ሕግ ሳትሠራ ፤ በሕገ ልቡና ሳሉ ጀምሮ ጾም መጾም በእብራውያን ዘንድ የተለመደ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። ከዚያም ወዲህ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ጾም ይጾሙ እንደነበር በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በብዙ ቦታ ተጽፎ ይገኛል ። አብዛኛውን ጊዜ የተለመደው ጾም ቢያንስ ከጥዋት አንሥቶ እስከ ማታ ድረስ እህል— ውሀ ሳይቀመስ በባዶ ሆድ መዋል እንደነበርም ታውቋል ።

የሚጾሙትም ጾሞች እንደሚከተለው በ፫ ታላላቅ ክፍሎች የተመደቡ ነበሩ ። እነሱም ፤

፩—ባጠቃላይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተመለከቱት ፤

፪—በረበናት (መምህራን)የተደነገጉት

፫—የግል ጾም ተብለው የሚታወቁት ናቸው ።

በብሉይ ኪዳን የታወቁት እንደ ገና ሲዘረዘሩ ፡—

፩—ዕለተ ሥርየት (ዮም—ኪፑር)

፪—ሀ/የመጀመሪያውና የሁለተኛው የቤተ መቅደሳቸው መፍረስ መታሰቢያ ጾም ፤

ለ/ የኢየሩሳሌምን ቅጽር መፍረስ በማስታወስ የሚጾሙት ጾም ፤

ሐ/ ኢየሩሳሌም በናቡከደነጾር መከበቧንና መወረሯን በማዘከር የሚጾሙት ፤

መ/ጾመ አስቴር ናቸው ። እኒህ አራቱ የጾም ዕለታት በትንቢተ ዘካርያስ ም/ ፰ ቁጥር ፲፱ ላይ ተመልክተዋል ።

ከፍ ብዬ ከገለጥኳቸው የጾም ዕለታት ውስጥ እንድትጾም ሕግ ሆና በቀጥታ ከጌታ የታዘዝዋት ጾም ፤ ዕለተ ሥርየት የምትባለው ብቻ መሆኗን አሪቱም ሆነ የታሪክ መጽሐፋቸው ያስረዳል ። አሪታውያን የዚችን ዕለት ጾም ፤ ዛሬም በታላቅ ቁም ነገር ይጠብቋታል ። ለ፳፬ ሰዓት ከእህል ከውሀ ተከልክለው በጸሎት ተጠምደው ከማናቸውም ተግባረ ሥጋ ተለይተው ያሳልፏታል ። በዚች ዕለት መታጠብ መቀባት ፤ መጫማት አይፈቀድም ። ሱቆች ፤ መደብሮች አይከፈቱም፤ የታጠቁትን ሳይፈቱ ፤ የፈቱትን ሳይታጠቁ እጅና እግር ኮርችም መዋል ነው ። በጥንቱማ ጊዜ የሚጾምዋት አመድ ነስንሰው፤ ማቅ ለብሰውነበር።

ታዲያ አፍአዊውን ሥርዓት ለመጠበቅ ይህን ያህል ሲተጉ ፤ ዋናውን ቁም ነገር ፤ የምሕረትና የይቅርታ ፤ የርኅራኄና የበጐነት ፤ የፍትሕና የርትእን ጉዳይ እንደሚገባቸው ሳይጠብቁ በመቅረታቸው ፤ ጌታ በነቢዩ በኢሳይያስ አድሮ ክፉኛ ወቅሶአቸዋል ። (ኢሳ ፶፰ ፤ ፮—፲፪)

ዕለተ—ሥርየት እንድትጾም የታዘዘው በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕ ፲፮ ከቁ ፳፱—፴፩ ባለው ክፍል ነው ። ትእዛዙም እንዲህ ይላል። «ይህም የዘለዓለም ሥርዓት ይሁንላችሁ ። በዚህ ቀን ትነጹ ዘንድ ማስተስሪያ ይሆንላችኋልና በሰባተኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን ራሳችሁን አስጨንቋት ፤ የአገር ልጅም በእናንተ መካከል የተቀመጠም እንግዳ ሥራን ሁሉ አትሥሩበት ፤ በእግዚአብሔር ፊት ከኃጢአታችሁ ትነጻላችሁ » ይኸው ትእዛዝ በ፳፫ኛው ም ከ፳፮—፴፪ ቁጥር ። ዘኁል/ ፳፱ ፤ ፯ ፤ በድጋሚ ተጽፏል ። ይሁን እንጂ አንባቢ እነዚህን ቁጥሮች ሲያገላብጥ ቢውል — በማናቸውም ቋንቋ ቢሆን በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጾም የሚል ቃል ሊያገኝ አይችልም ። ነገሩ ግን እንዲህ ነው። በቋንቋቸው (ዕብራይስጥ) ስለጾም የሚገልጹ ሁለት ተመሳሳይ ቃላት አሉ «ጹም» እና «ኢንሐ ነፍስ»ተብለው ይታወቃሉ ። ጹም የቃል— በቃሉ ትርጉም ጾም ማለት ሲሆን ፤ ኢንሐ ነፍስ ማለት ግን ፤ « ነፍስን ማስጨነቅ» ማለት ነው ። ነፍስን ማስጨነቅ መፀፀት ፤ ማዘን ፤ ማልቀስ ማለትም ያው ጾም ማለት መሆኑን የታሪክ መጻሕፍት ያስረዳሉ ፤ እነ

ወደ ገጽ ፰ የዞረል



# ክርስቲያናዊ ሕይወት

## መከሩ ብዙ ነው ሠራተኛው ግን ጥቂት ነው

በአገራችን በኢትዮጵያ ምን ጊዜም መከር ነው ቢባል ስህተት አይመስለኝም ፤ ምክንያቱም የመከሩ ሲታጨድ የበልጉ ይዘራል ፤ የበልጉ ሲታጨድ የመከሩ ይዘራል ፤ እንደኛው ወገን የደረሰውን ሲሰበስብ ሌላው ወገን ደግሞ እየተከተለ ማረስና ለዘር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤ስለዚህ ብዙ ሠራተኞች ከተሰለፉ ብዙ ማምረት ይቻላል አገራችን በተፈጥሮ በጂኦግራፊ አቀማመጥና የአየር ንብረት የታደለች ተክል ለመትከል ዘር ለመዝራትና ከብት ለማርባት አመች ናት ፤ ግን ምን ይሆናል ቅድመ አብዮት በመሪዎቻችን ራስ ወዳድነት ፤ በብዙኃኑ ሕዝብ አለመማርና አለማወቅ ምክንያት መችግር ሳይገባን ስንቸገር ፤ መራብ ሳይገባን ስንራብ መታረዝ ሳይኖርብን ስንታረዝ ኖረናል ፤ ለወደፊቱ ግን አሁን የጀመርነው የትምህርትና የምርት ዘመቻ ብዙ ሳይዘገይ ግቡን ይመታል ዕውቀታችን ይዳብራል ፤ ምርታችን ያድጋል ችግርና ድንቁርና ሁሉ ከኢትዮጵያ ይወገዳል ብለን እናምናለን ።



በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የፈለግሁት ስለ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ለምነትና የአየር ንብረት ሁኔታ አይደለም ፤ ምክንያቱም ስለ መዓድናት ስለ እርሻናስለ ምርት ጥናት በሙያው የሰለጠኑ ሊቃውንት ስላሉ ለእነርሱ መተው የበለጠ መሆኑን በመገንዘብ ነው ።

በዚህ መነሻ ለመግለጽ የምፈልገው የክርስትናን ሕይወት የመሠረተው መድኃኒታችን ክርስቶስ «መከሩስ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው ወደ መከሩ ሠራተኞችን ይልክ ዘንድ የመከሩን ጌታ ለምኑት ሲል ለሰዎች የሰጠውን መመሪያ ነው ፤ ከዚህም የተነሳ መከሩ ምን ዓይነት መከር ነው ? ሠራተኞቹስ እነማን ናቸው ? ስለምን ጥቂቶች ሆኑ የመከሩስ ባለቤት ማን ነው ? ብሎ ለመጠየቅና ለጥያቄዎቹ መልስ ማግኘት ለክርስትና ሕይወትና ለሰው ልጆች አቅምም አስፈላጊ መሆኑን ነው ።

አዎ መከሩ የሰው ልጅ ሁሉ ነው እርሱንም በሶስት መደብ መድበን ለመመልከት እንሞክራለን እነርሱም ፡-

፩ኛ/ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ፤ የትምህርትን ብርሃን ካለማየታቸው የተነሳ በድንቁርና ጨለማ ተውጠው፤ በችግር ተጐሳቁለውና በልዩ ልዩ ደዌ ተጠቅተው የሚታዩት ወገኖች ናቸው፤ እነርሱም እስካሁን እስከ ሐያኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ላለው ከፍተኛ ዕውቀት እንኳን ቢቀር ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ፤ ሠርቶ የመኖር መብትና ችሎታ ሳያገኙ የኖሩት ትክክለኛ መሪ እውነተኛ አስተማሪ ሰብሳቢ ሠርቶ የሚያሠራ በማጣት እንጂ በራሳቸው ስንፍና እንዳልሆነ ግልጥ ነው ፤ ታዲያ እነዚህን ሁሉ ከወደቁበት የኑሮ ጨለማ አውጥቶ የዕውቀትን ጭላንጭል እንዲያዩና እናት አገራቸው ከእነርሱ የምትፈልገውን እነርሱም ከእናት አገራቸው የሚፈልጉትን ከሚያውቁበት ደረጃ ደርሰዋል ።

ይህን የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው ሠራተኞችም በብዙኃኑ ሕዝብ ገንዘብ ተምረው የዕውቀት ብርሃን ያዩሁሉ ናቸው ። የመከሩ ባለቤቶችም መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ናቸው ፤ መን



www.ethiopianorthodox.org

ግሥትና ቤተ ክርስቲያን የሰለጠነውን እያበረታቱ ያልሰለጠነውን እያሰለጠኑ ግዴታውን በማሳወቅ የባለሙያዎች ቍጥር በጥራትም ሆነ በብዛት በየጊዜው እንዲጨመር ያደረጉ እንደሆነ ወደ መከሩ ሠራተኞችን ላኩ ማለት ነው ።

፬ኛ/ ተምረውም ሆነ ሳይማሩ ግብረ ገብነት የጐደላቸው (ሞራላቸው የወደቀ)ወገኖች ናቸው ፤ የግብረ ገብነት ትምህርት የሰዎችን ጠባይ በትክክል የሚመራ ጥበብ ነው ። ለምሳሌ አንድ ተሽከርካሪ አቅጣጫውን በትክክልና በቀጥታ ከያዘ ሞተሩም ካልተበላሸ በሚገባ መንገዱን ያከናውናል ተሳፋሪዎቹንም ከአደጋ ላይ አይጥልም ፤ ነገር ግን አቅጣጫውን ከሳተ ፤ ወይም ከሞተሩ ብልሽት ከእሰ አደጋ ይደርስበታል ፤ የግብረ ገብነት (የሞራል)ሕግ ሰውን የሚመራ ሞተር ነው ፤ ይባላል ይሁን እንጂ ብዙዎቻችን ግብረ ገብነት ጐድሎናል ፤ ለስካር ለዝሙትና ለመሳሰሉት ርካሽ ልማዶች ተገዢች ሆነናል ። ከዚህም የተነሣ የሥራ ሰዓትን ባለማክበር የተመደብንበትን ሥራ በጊዜው ባለማከናወን ፤ ሥራንና አገርን የምንበድል ጥቂቶች አይደለንም ከዚህም ሌላ የምናገኘውን የወር ገቢ መጠን በሌላ መጥፎ ልማድ በማባከን ቤተ ሰብን የምናስርብ ኀብረተ ሰቡን የምናስቸግር እንታጣም ይህን ሁሉ ለማረምና ለማስተካከል ግብረ ገቦች ሁሉ ሠራተኞች ናቸው ።

አንድ ሰው ግብረ ገብ የሚባለው ሲፈጽመው የሚገባውን ሁሉ በፈቃዱ አውቆ ሲፈጽም ነው ። ግብረ ገብነት የጐደለው ነው የሚባለውም ሊያደርገው የሚገባውን በሙሉ ሳይፈጽም ሲቀር ነው በተቻላቸው መጠን ለሰው ዘር ሁሉ መልካም የሚያደርጉና ባልንጀሮቻቸውን እንደ ራሳቸው የሚወድዱ ግብረ ገቦች ናቸው ያላቸውን ችሎታ ለኅብረተሰብእ አገልግሎት የሚያውሉና ለሥራ የሚተጉ ሁሉ ለእኔ ብቻ የማይሉና በእኩልነት የሚያምኑ ግብረ ገቦች ናቸው ። ታዲያ እንዲህ ሆነው የሚገኙት በቍጥር አነስኞች ስለሚሆኑና ከዚህ ውጭ የሆኑት ቍጥር ደግሞ ስለሚበዛ «መከሩስ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው» አለ የመከሩንና የሠራተኞችን ሁኔታ የተመለከተው መድኃኒታችን ክርስቶስ ፤

፭ኛ/ የእግዚአብሔር ቃል ያልደረሳቸው ወንጌል ያልተሰበከላቸው ፤ የሥጋና የመንፈስ በሽታ ድንቁርና ያሸነፋቸው ብዙዎች ነበሩ ፤ የእኩልነትና የክርስትናን ሕይወት የመሠረተው መድኃኒታችን ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ እየዞረ ያስተምር ነበር ፤ ሲያስተምርም በበሽታ ለተጠቁት ፈውስ ፤ በችግር ለተያዙት ምግብና ልብስ በመስጠትነበር ፤ ይህን እያደረገ ከመንደር ወደ መንደር ከከተማ ወደ ከተማ ሲዘዋወር ፤ የታመመውን የሚያክም ፤ ያዘነውን የሚያጽናና ፤ የተራቆተውን የሚያለብስ ፤ የተራበውን የሚመግብ ፤ የሰነፈውን የሚያተጋ ፤ ያልተማረውን የሚያስተምርና በልዩ ልዩ ምክንያት ግብረ ገብነት የጐደለውን (ሞራሉ የወደቀውን) በትምህርት የሚጠግን ማንም አልነበረም ብቻብዙ ሰዎች እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተተጥለውና ተጨንቀው አየ ሁኔታው አሳዛነው ስለዚህ «መከሩስ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው» አለ አሁንም ቢሆን የሥጋና የነፍስ ደዌ ከሆነው ከድንቁርና ለመውጣት ትምህርት ፤ከልዩ ልዩ ሱስና ልማድ ለመላቀቅ ንቃት ግብረ ገብነትና የእግዚአብሔር ቃል የሚያስፈልጋቸው ብዙዎች ናቸው ስለዚህ በብዙኀኑ ሕዝብ አስተዋጽኦ የተማሩ ሁሉ ብዙኀኑን ሕዝብ የማስተማር ፤ የማንቃትና እነርሱ ያዩትን የዕውቀት ብርሃን ለሌሎችም የማሳየት ግዴታ አለባቸው ።

ሰዎች ከችግር ተላቀው ምቾትን ፤ ከበሽታ ድነው ሕይወትን ፤ ከድንቁርና ወጥተው ዕውቀትን ፤እንዲያገኙ ለሚደረገው ጥረት በክርስትና ሕይወት የሚኖሩ ሁሉ ግንባር ቀደም መሆን ይኖርባቸዋል ። ምክንያቱም በክርስትና ሕይወት ለሌሎች መልካም ከማድረግ የበለጠ ደስታ የለምና «ሠራተኞች ጥቂቶች ናቸው» የተባለበትም ምክንያት የተማሩ ሰዎች ቍጥር ማነስ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ሰው ያለውን ዕውቀት ጉልበትና ችሎታ ለኅብረተ ሰብእ አገልግሎት ለማዋል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጭምር እንደሆነ ያመለክታል እያንዳንዳችን እኛ የምናውቀውን ለሌላው የምናስተምር እኛየሰማነውን ለሌላው የምናሰማ ፤ ለእኛ ያለን ለሌሎች እንዲኖራቸው ለማድረግ ፈቃደኞች ከሆንና ለሥራ ከተሰለፍን ሠራተኞች አያንሱም ፤ መከሩም ይሰበሰባል እንዲህም ከሆነ የመከሩ ጌታ በመከሩ መሰብሰብ ይደሰታል ለሠራተኞቹም እንደ እየሥራቸው መጠን ዋጋቸውን ይከፍላል ።

ስለዚህ ለሠራተኞች ጉልበትን ትጋትንና የሥራ ክንውንን ፤ ለመምህራን ምስጢር መመርመርን ኃይለ ቃል መተርጐምን እንዲሰጥ የመከሩን ባለ ቤት ክርስቶስን በጸሎትና በእምነት መጠየቅ ያስፈልጋል ። በዚህ ሁኔታ ሠራተኞች ዕለታዊ ሥራቸውን በትጋት ከአከናወኑ መምህራን ተፈላጊውን ትምህርት ለሕዝብ ከአዳረሱ የክርስትና ሕይወት ትክክለኛ ትርጉም ይይዛል ።


ራደ አስረስ ።



# የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች

ካለፈው መጽሔት ቁ. 23 የቀጠለ ክፍል 3

ከአሁን በፊት እንደገለጽነው ሁሉ የቅዱሳት ቦታዎች ባለመብቶች ግሪክን ተከትለው በቀደምትነት የታወቁ ኩርጅና ሐበሽ ናቸው የሚለውን ተመልክተናል ። ስለዚህ የኩርጅና የሐበሽ ገዳማት በየክፍሉ የነበሩ ቦታዎች ብዙ ስለሆኑ ከእነዚሁ ከታወቁት ቦታዎች አንዱ ዴር ማር ያዕቆብ ( ያዕቆብ ገዳም ) በመባል የታወቀው ነበርና አርመኖች ይህንኑ ቦታ በ፲፰፻፷፫ ዓ.ም. በ፹ (በሰማኒያ)




በካርታው ላይ የተከበበው ቦታ በዴር ሡልጣን የኢትዮጵያን ይዞታ ያመለክታል ።

ዲናር ተከራይተው ገቡበት ይህንኑ እየከፋፈሉ እስከ ፲፰፻፺፩ ዓ.ም.ቆይ ተው ኩርጅን ፊጽመው በማስወገድ ኢትዮጵያውያንንም በልዩ ልዩ ዘዴ በማዳከም ጠቅላላ መብትና ኃላፊ ነት በአርመኖች ሆነ ይህም ታሪክ ከኒሳት ኢሩሻሌም ገጽ ፩፻ እስከ ፩፻፺፩ በሰፊው ተጽፎአል አሁን የም ንፈልገው በቅዱስ ቦታ የሚነሳውን ጭቅጭቅ ለማብረድ በቱርክ መን ግሥት ዘመን እስታቲክ ( ይርጋ ) የተባለው ውሳኔ ፀጀርመን ሀገር የዓ ለም ኅብረት ከጸፀደቀው በኋላ እነ ዚህ ከላይ የተጠቀሱት የአርመንና የግብጽ መነኮሳት በኢትዮጵያውያን መብት ላይ እየገቡ የሚፈጽሙት ግፍ ሲቆም ባለመቻሉ ቡርትስ ሽክ የተባለ የጀርመን መሐንዲስ በ፲፰፻ ፷፰ ዓ-ም በጻፈው መጽሐፍና በአ ነሳው ካርታ በገጽ ፩፻ ላይ የተጠቀ ሰው ቃልና ከእንሳውም ካርታ ላይ የሚያመለክተው ቦታና የሚዘረዝ ረው ቃል የሚከተለው ነው ። የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የኢትዮ ጵያውያን ርስት ነው ከአለ በኋላ ይህ የተጠቀሰው መሐንዲስ የጐልጐታን ሁኔታ የሚያሳይ በአውጣው ካርታ ላይ በልዩ ልዩ ዓይነትና መልክ አድርጐ ሲሰራና ስሙን ሲሰጥ የሰጠው የካርታ መልክ የሚከተለው ነው ግብጾች ያሉበት በብርቱካን መልክ ቀለም ነው ። የሐበሾችም ቦታ በራ ባለ ቅጠልያ ቀለም ነው ። የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንም በቤተ ክርስቲያኑም ጥግ የምትገኘ ው ትንሽ ቤት በእውነቱ የኢትዮጵያ ርስት ናት ይላል ። ነገር ግን መሐን ዲሱ በካርታ የኢትዮጵያን በሚያመ ለክተው ቀለም ሲያነሳ ሲያመለክት በካርታው ላይ ትቷታል ። ምክንያ ቱም በዚህ ሰዓት ይህች የተጠቀሰ ችውን ቤት በግሪኮች እጅ ስለ አገ ኛት መልኳን በግሪኮች ቀለም ሲያ ነሳ ምክንያቱን ደግሞ የኢትዮጵያ ርስት ናት ብሎ ጽፏል ። የዚሁ የተጠ ቀሰው መሐንዲስ ካርታ ቦታውን ሁሉ በእያንዳንዱ እየለየ ሲያነሳ በተጠቀሰው ሰዓት በሐበሾች እጅ የነበረውን ሁሉ በግልጽ ዘርዝሮ ያስ ረዳል የቀለሙንም ልዩነት በግልጽ ያሳያል ። ይህ ካርታ መሐንዲሱ ከአነሳው በኋላ በኢትዮጵያውያን ተግቶ አለመከታተል የግብፅ መነኮ ሳት ይህን የተጠቀሰውን ቤተ ክርስ ቲያን ያለ ሕግ እውነትን አጥፍተው የግል ጥቅም ለማዳበር ሲሉ በራሳ ቸው ሥልጣን ዘግተውት ነበር አሁን ግን በሙሉ ባይመለስም በሕግ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቷል ።

ካርታውም ከላይ እንደተጠቀሰው የቀለም መልክ በዚሁ ክልሼ ተስተካ ክሎ ባለመገኘቱ በተለይ የኢትዮጵ ያውያን ክፍል በጥቁር ቀለም ዓይ ነቱ ተመልክቷል ደግሞም የቦታው ቅርጽ በጣም የተቀራረበ ሆኖ የሚ ታየው ነው ። መጀመሪያው በጐ ልጐታ በር የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከፍ ብሎም የአርባዕቱ እንስሳ ቤተ ክርስቲያን ቀጥሎም ትና ንሽ ቤቶች የሚታዩበት ነውና አጥ ብቃችሁ በካርታው ላይ የሚታየውን ምልክት ተመልክታችሁ ተረዱ ።

(ይቀጥላል)

መምህር ኪዳነ ማርያም ገ/ሕይወት ።

# ይህን ያውቁ ኖርዋል ?

ከ፬ኛው ገጽ የዞረ

ርሱም ቅሉ ዛሬም በተግባር ሲፈጽ ሙት ይታያሉ ።

የቀሩት በ፪ተኛው ተራ ቁጥር የተ ዘረዘሩት አጽዋማት ግን ፤ ኢየሩሳ ሌም በባቢሎናውያን እጅ ከወደቀች በት ከ፭፻፹፮ ዓ/ ዓለም ጀምሮ ከታ ሪካቸው ውስጥ የተፈጸሙትን ዋና ዋናዎቹን አሳዛኝ ድርጊቶች በማሰ ብ በማዘንና በማልቀስ ፤—ነፍስን በማ ስጨነቅ ፤—በተሰበረ መንፈስ) የሚ ጾምዋቸው ናቸው ። እነሱም አራት ዕለታት ናቸው ። (ዘካ ፰ ፤ ፲፱)

በረበናት (መምህራን) የተደነገጉ አጽዋማት ብዙዎች ሲሆኑ ፤ ከእነዚ ህም ውስጥ ፤ የሰኞና የሐሙስ ጾም ይገኙባቸዋል ። እኒህም ፈሪሳዊው «በሳምንት ሁለት ቀን እጾማለሁ ፤» ሲል የተመጻደቀባቸው ናቸው ። ሉቃ ም ፲፰ ፡ ፲፪

የግል ጾም የሚጾምባቸው ምክን ያቶች አያሌ ናቸው ። ሁሉንም ለመ ዘርዘር ያዳግታል ሙሴ ፤ ኤልያስና ዳንኤል እያንዳንዳቸው የጾሙት ጾም መደቡ ከግል ጾም ውስጥ ነው ።

ከዚህም በቀር በሀገር ላይ ረሃብ— ቸነፈር በሕዝቡም ላይ መቅሠፍት ሲታዘዝ የይቅርታና የምሕረት መጠ የቂያው መንገድ ጾም መሆኑ ተጽፏል ሕፃናትና እንስሳት እንኳ ሳይቀሩ የጾ ሙበት ጊዜ አለ ። ዮና ም ፫ ፤ ቁጥር ፯

ጾም ከጸሎትና ከበጎ ሥራ ተለይቶ ብቻውን ሊፈጸም እንደማይገባው የታወቀ ነው ። ኢሳ- ፶፰ ፤ ከቁ- ፮— ፰ ዘካ ም ፯ ፤ ከቁ/፩—፲፩ ። )

በነገራችን ላይ ጾም የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስንት ጊዜ እን ደተጠቀሰ ያውቃሉ ? በሐዲስስ ? በብሉይ ፴፬ ጊዜ ፤ በሐዲስ ፲፰ ጊዜ በጠቅላላው ፶፪ ጊዜ ተጠቅሷል ። ፸፯ ጊዜ የሚሉም አሉ ። ይህም ፤ «ነፍስን ማስጨነቅ » የምትለዋ ሐረግ አብራ ተቆጥራ መሆኑ ነው ።

በሚቀጥለው ጊዜ ጾም በክርስትና እምነት ውስጥ ስላለው ትርጉም ለመ ግለጥ እሞክራለሁ ።

ምስክረ መጻሕፍት ።

፩—መ/ ቅዱስ ፤

፪—አዲሱ የመ/ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አይ ቢ- )

፫—ኢንሳይክሎፒዲያ ጁዳይካ ፤

፬— » ብሪታኒካ ፤



# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፡ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፡ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።



አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቁጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ

በትዳር ከተወሰንኩ ፲፰ ዓመታት አል ፈውኛል ፤ ይሁን እንጂ ባለቤቴ መጀ መሪያ ሲያጨኝና ካገባኝም በኋላ ለጥ ቂት ዓመታት ያሳየው የነበረው መል ካም ጠባይ ተለውጦ ዛሬ ይሠክራል፤ ያመሻል ፤ ከዚህም አልፎ ከውጭ ያድራል ።

በዚህ የጋብቻ ዕድሜያችን ሰባት ልጆች ወልደናል ። ባለቤቴ የሚያገ ኘው ደመወዝ ከፍተኛ ቢሆንም ስለ ሚሰክርበትና ስለሚያባክነው ለቤት ወጭ አይሰጠኝም ።

ስለዚህም ከነልጆቼ በከባድ ችግር ላይ እገኛለሁ ። እኔ ሥራ ገብቼ ችግ ሬን አቃልላለሁ እንዳልል ትምህር ቴን ሳልገፋ ስለአቋረጠኝ በቂ ችሎታ የለኝም ።

ስለዚህ በጣም ተቸግሬአለሁና ምክ ርህን ትለግሰኝ ዘንድ ዓምድህን እጠ ባበቃለሁ ።

ከአ/አ

ስሜን ደብቅልኝ ፤

ከአዘጋጁ ፤ ይህ ዓይነቱ አድራጐት ዛሬ በብዙ ሰዎች ዘንድ የሚታይና የደ ረሰም ነው ።

ብዙ ጊዜ እንደሚታየው ጉድለቱ የወንዶች እንደሆነ ይገመታል ። ወን ዶቹ ገንዘብ በእጃቸው ስለሆነ ጥቂት በጥቂት መጠጥ ይለምዱና የዘወትር ሱሰኞች ሊሆኑ ይችላሉ ።

ታዲያ እንዲህ ዓይነቶቹ ወንዶች የመጠጥ ሱሰኞች ሊሆኑ የሚችሉት ፩ኛ ከወንደላጤነት ጊዜያቸው ጀምሮ ሲሆን እንዲህ ዓይነቶቹ ወንዶች የመጠጥ ሱሳቸውን ለማርካትና እን ደፈለጉም ፤ ለመሆን ሲሉ ቶሎ በት ዳር ለመወሰን አይሞክሩም ።

በመጨረሻም በትዳር ለመወሰን ሲሞክሩ በየመጠጥ ቤቱ ከለመዱ ዋቸው አንዷን ሲመርጡና በሞቅ ታም ጊዜ ሲያገቡ ስለሚችሉ በሁለቱ መካከል በሚኖረው አለመተማመን ምክንያት ቢጠጣም ባይጠጣም ጠጥ ተሀል ፤ አምሽቶ ከገባ በገዘሙት ቢወ ድቅም ባይወድቅም ዘወትር በገዘሙት እንደሚባልግ አድርጋ ስለምትቆጥ ረው ዘወትር ንዝንዝ ጭቅጭቅ ነው በእንዲህ ዓይነቱ ትዳር

ይህ አንዱ ዓይነት የትዳር ነቀርሣ ነው ሌላው ደግሞ ፤ በሴቶች አካባቢ የሚመጣ ጉድለት ነው ይባላል ።

ይኸውም አንዳንድ ሴቶች ከቤት ለባ ሎቻቸው ምንም ዓይነት አጠባበቅና እንክብካቤ ስለማያደርጉ እንዲሁም በምግብ በኩል ስለማይመቹው በዚህ ምክንያት በግድ የውጭ እጅ ይለ ምዳል ። በኋላማ ቁርስ ውጭ ፤ ምሳ ውጭ ራት ውጭ ፤ ቀስ በቀስ አዳርም ውጭ ይሆናል ።

በእውነቱ በጥናት እንደተደረሰበት የሴቶች ጠባይ አለመስተካከልና ለባ ሎቻቸውም እንክብካቤ ካለማድረጋ ቸው የተነሳ ብዙ ትዳሮች መፍረሳ ቸው ይነገራል ።

አንድ የሚነገር አፈ ተረት አለ ይኸ ውም « አንዲት ሴት አንድ ጊዜ ወደ አንድ ሰው ሂዳእባክዎ ባሌ በምሳ ቤት አይገባም ስለዚህ ለዚህ ነገር መፍትሔ ይፈልጉልኝ ከቤቱም እንዲመገብ የሚደረግበትን ዘዴ ይፍጠሩልኝ ትላ ቸዋለች ።

ሰውየውም ሲመልሱላት ከቤት የምታቀርቢለትን ምግብ አዘጋጂና አንድ ቀን ጥሪኝ እርሱም በዚሁ ዕለት እንዲገኝ አድርጊ ይሏታል ።

እርሷም የተላመደውን አሽር ባሽር ዘይቱ ሳይቁላላ ሺሮውና ውሃው ሳይ ስማማ በጠቅላላ አረፋው ኩፍ ኩፍ እያለ እንደከረምት ጉም እያንዣበበ ታቀርበዋለች በዚያን ጊዜ እንኳን ባለቤቱ እንግዳውም ለመቅመስ ይቸ ገራሉ እርሳቸውም ፤ ገንዘብ አንሷት ነው እንዳይሉ ችግሩ የገንዘብ ጉዳይ ሳይሆን የቀረበው ወጥ የተጣላው ከእ ሳት ጋር ነው ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ባል በየቀኑ የሚ መገብበትን ሆቴል በመጠየቅ እርሷን እስከ ትለው በምሳ ሰዓት ይሄዳሉ ከዚ ያም ባል ቀርቦለት የሚመገበውን



www.ethiopianorthodox.org

ምግብ ዓይነት አስቀርበው ሶስቱም ባንድነት ከተመገቡ በኋላ ለሴትዮዋ በሰጡዋት ምክር ባልሽ አልበላ ያለው ምግቡ ስለአልተስማማው ነው ።

ሌላው ቀርቶ የምታቀርቢውን ምግብ እሳት እንኳን በደንብ ቢመታው ሊመ ገብ ይችላል እኔ ላንድ ቀን እንኳ አል ዋጠኝ ያለ ዘወትር እርሱ ሊመገበው አይችልም ።

ስለዚህ ምግቡን አሻሽይ እርሱ ዛሬ በየቡና ቤቱ ከሚመገበው የተሻለ አድ ርገሽ ካቀረብሽለት ፤ ለቤቱም ባያስብ ለምግቡ ሲል የምሳ ሰዓት ሊያከብር ይችላል ይሏታል ። እርሷም በተሰጣት ምክር ተጠቅማ ለባሏ የምታደርገውን እንክብካቤና የምግብ አቀራረብ ስለ አሻሻለች ባሏ ወደቀድሞ ኑሮው ተመልሶ ሊፈርስ የተቃረበው ቤታ ቸው እንደገና ሊገነባ ቻለ ይባላል ።

ስለዚህ እርስዎም ምን አልባት ያል ተግባባችሁበት በምን እንደሁ ባል ረዳውም በዚህ በኩል ጥንቃቄ ቢያ ደርጉ መልካም ነው ። ዘወትር ፈገግታ አይንፈጉዋቸው የሚበሳጩበትን ነገር በተቻለ መጠን ለማንሳት ወይም ለመፈጸም አይሞክሩ ። ከውጭ የሚወ ዱትን ነገር በተቻለመጠን ከቤት እንዲ ገኙ ለማድረግ ይጣሩ ምንጊዜም በፍ ቅር ዓይን እንጂ በንቀት መንፈስ አይ መልከቱዋቸው ። ጠጥተው ሲገቡም ጭቅጭቅ የሚያነሱበትን ነገር እያስ ታወሱ እርስዎም ሞራላቸውን የሚ ነካ ፤ ስካራምነታቸውንም የሚያሳ ውቅ ነገር አይናገሩ ።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ቤታቸውን እንዳ ያፈቅሩ የሚያደርጋቸው ሌላ ምክን ያት እንጻለም ለማስወገድ ይሞክሩ ከዚህ በኋላ መልካም ኑሮ ለመኖር ትችላለሁ ልጆቻችሁንም በመልካም ሁኔታ ለመያዝ ትበቃላችሁ ። ሥራ ለመያዝ ችሎታ የለኝም ስለሚሉት ሥራ በትምህርት ብቻ የሚገኝ ሳይ ሆን ብዙ የሞያ ሥራዎች ስለአሉ በአንዱ ተሰማርተው ለመሥራት ይሞ ክሩ በትርፍ ጊዜዎም እየተማሩ ችሎ ታዎን ለማሻሻል ይጣጣሩ ። ጊዜው ሁሉ የሚማርበት የትምህርት ጊዜ ነውና ።

---

# ደብዳቤዎች

ከ፱ኛው ገጽ የዞረ

ስዋም ወዳኛለች ። ግን በቂ ሥራ ስለሌለኝ እርስዋን በመተው ትምህ ርቴን ቀጠልሁ ። ይሁን እንጂ እርስዋ አስቸገረችኝ ። ምናልባት አስደስቻት ይሆናል በማለት በመጠኑ ልቀርባት ቻልሁ ። ለጥቂት ጊዜ አብረን እየተ ማርን ሥራ ስይዝ አገባታለሁ እያልሁ ሳስብ በመካከላችን ልዩነት መጣ ። እኔ ግን በፍቅርዋ ተያዝሁ ጥፋቱ ከሁ ለታችንም ይሆናል በማለት በደብ ዳቤ ወይም በቃል እንድትነግረኝ ጻፍ ሁላት እርስዋም ሳትነግረኝ ቀረች ። ይባስ ብላ እኔን የሚያበሳጭ ድርጊ ቶች ትፈጽም ጀመረች ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ለማነጋገር ፈለገች ። እኔም ስለ ተበሳጨሁ ዝም አልኋት አሁን ከእርስዋ ጋር ያለኝ ፍቅር በመ ጠኑ ስለለቀቀኝ እርስዋም እንደ እኔ በመሆንዋ ምን ማድረግ ይሻለኛል ?

አካሉ አመኑ ።

የካ ሚካኤል ፖስታ ቤት ወኪል

አዲስ አበባ

● አቶ አካሉ አመኑ በቅድሚያ ሰላ ምታችንን ይድረስህ ፍቅር ያሳደረች ብህ ልጅ ክርስቲያን ናት ? አንተ ራስህ ግን ክርስቲያን መሆንህን በደ ብዳቤህ አቀራረብ ተረድተናል ። ይህን ማለታችን የክርስቲያኖች ፍ ቅር ሥጋዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊም መሆን አለበትና ነው። ደግሞም ትምህ ርትህን ከመፈጸምህ በፊት ትምህ ርትዋን ካልፈጸመች ልጅ ጋር ሥጋዊ ፍቅር አያይያዝህ ። ከዚህም ሌላ በቂ ሥራ የለኝም ብለሀል ። ለመሆኑ እርስዋ እስከ መጨረሻው ብታፈ ቅርህና ብታገባት ያለበቂ ሥራ በምን ልታስተዳድራት ኖሯል ? የአንተም የርስዋም ኑሮ የተሳካ አይሆንም ነበር። ምናልባት እርስዋም ገለል ያደረገ ችህ የትምህርትህን አለመጨረስና በቂ ሥራ የሌለህ መሆንህን አይታ ይሆናልና ትምህርትህን ለመፈጸም ታገል ትምህርትህንም ከፈጸምህ በቂ ሥራ እንደምትይዝ ሙሉ ተስፋ ይኑርህ ከዚያ በኋላ ዛሬ የጠሉህ ይወዱሀል የፍቅር ደብዳቤም ይጐር ፍልሀል ፡ ታዲያ ያንጊዜ እንዳትከ ራባቸው አስተውል ።

✶ ✶ ✶

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፤

በቁጥር ፳፩ ታትሞ በወጣው ትንሳኤ መጽሔት የመምህር ኪዳነ ማርያም ገ/ ሕይወ ትን መርሐ አዝማን በማስመልከት ከአባ ተክለ ድንግል ደሴ የቀረበውን ጽሑፍ ተመልክቻለሁ ። ፍሬ ነገሩንም ስመለከተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሱባኤ ነቢያትና በቀመረ ሊቃውንት የም ትመራ መነሻና መድረሻ ያላት መሆ ኑን ጠቁሞ የመምህር ኪዳነ ማርያም መርሐ አዝማን ከስምንት ሺህ ዓመት አልፎ በመሔዱ ጭንቀት የፈጠረባ ቸው ስለሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ነው ? ወይስ የሳይንቲስቶች የሚ ለውን ጥያቄ እንዲያቀርቡ የተገደዱ መሆናቸውን ያሳያል ። ይሁን እንጂ ጠያቂው ተመልሰው ተጠያቂ መሆ ናቸው አልቀረም ምክንያቱም ቀደም ሲል በቅድስት ሥላሴ ገዳም አማካይ ነት የታተመው አቡሻክር ከ፲፱፻፷፪ ጀምሮ ያለ ማቋረጥ እስከ ፲፻፬፻፹ ዘመን ይቆጥራል ። የአለቃ ጌታሁን መርሐ ዕውርም ከ፬፻ ዓመተ ዓለም እስከ ፱፻፹ ዓመተ ዓለም ብቻ ይቆ ጥርና ተፈጸመ ይላል ይኸውም አስተሳ ሰብ ዘመነ ሥጋዌን ወይም ዓመተ ምሕ ረትን ሳይነካ ተፈጸመ ማለቱ እንደ ሆነ ጠያቂንም መልስ ሰጭንም ያስ ቸግራል ሆኖም አባ ተክለ ድንግል በሌሎቹ ሐሳብ ተስማምተው በመም ህር ኪዳነ ማርያም ሐሳብ አልተስማ ሙም እንደሆነ ልዩነቱን አልገለጹም በሌላ በኩል ደግሞ ያየሁት ይህን ብቻ ነውና ይኸንኑ መተቸት አሰብኝ ብለው እንደሆነ በዚያው መንገድ ልምጣና የመምህር ኪዳነ ማርያም መርሐ አዝማን ከሱባኤ ነቢያትና ከቀመረ ሊቃውንት ጋር ያልተስማ ማው በምን ነጥብ እንደሆነ ፤ ከሳይ ንሱ ጋር ይስማማል ብለው ካሰቡ ደግሞ የሚስማማው በምን ነጥብ እንደሆነ ፤ ባለቤቱ ራሱ ያልወሰነ ውን ምዕአት በስምንተኛው ሺህ ዘመን ነው ብሎ የወሰነው ማን እንደ ሆነ በነካ አፋቸው እንዲያብራሩልኝ ይህን ጥያቄ አቅርቢያለሁ ይህን አብራ ርተው ባቀረቡ ጊዜ መልስ ለመስ ጠት ዝግጁ ነኝ ።

ወረታ ለማ አ-አ

● አቶ ወረታ ለማ ለጥያቄው መልስ መስጠት ሲገባዎ መልሰው ጥያቄ አቅ ርበዋል ። መጽሔታችን የትምህርት መስጫ እንጂ ማከራከሪያ አለመሆኑ ንም ልንገልጥልዎ እንወዳለን ። ይህን ጥያቄ ከማቅረብ ይልቅ ትክክለኛ መልስ ይሆናል ብለው የሚያምኑበ ትን ሐሳብ ቢያቀርቡ ኖሮ ብዙዎች አንባቢያን ይደሰቱ ነበር ። እንግዲህ አባ ተክለ ድንግል ለርስዎ ጥያቄ ከመለሱ በኋላ እርስዎ ሊመልሱ ነው ማለት ነው በዚህ ጊዜ የመጀመሪያው ሐሳብ ፈጽሞ ተዘንግቶ እንደሚቀር ያስተውሉ ።

★ ★ ★

ለትንሳኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅዳሴ ጊዜ የግል ጸሎትና መንሸ ራሸር እንዲቆም ለምን አይደረግም ከዚህም ጋር በዕለተ እሑድ ቅዳሴ ተቀድሶ አሜን ከተባለ በኋላ ለ፴ ደቂቃ ያህል ለምዕመናን ትምህርት ለምን አይሰጣቸውም ?

ሰሎሞን ወ/ትንሣኤ አዲስ አበባ

● አቶ ሰሎሞን ወ/ትንሣኤ እኛም በርስዎ ጥያቄ እንስማማለን ፤ በቅዳሴ ጊዜ ቅዳሴው ራሱ ማንኛውም ክርስ ቲያን የሚካፈለው ጸሎት ነው ለምሳሌ ዲያቆን «ጸልዩ» ሲል ሕዝቡ አቤቱ ጌታሆይ ይቅርበለን ፤ ቄሱ ሰላም ለሁ ላችሁ ሲል ሕዝቡ ከመንፈስህ ጋር ይላሉ ። ታዲያ በዚህ ጊዜ የግል ጸሎት መያዝ አይገባም ፤ ጉድለቱ የካህናት ይመስለኛል ። ምክንያቱም ተሰጥዎ እንዲቀበሉ ለሕዝቡ አላስተማሩምና ስለዚህ አንዳንድ ምዕመናን በዝምታ ከመቆም የግል ጸሎት ሲጸልዩ ይታ ያሉ ካህናት ለሕዝብ አስተማሪዎች ናቸውና በቅዳሴ ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባ ለሕዝቡ እንዲያስተምሩ በዚህ አጋጣሚ እናሳስባለን ።

ከቅዳሴ በኋላ ስለአለው ትምህር ትም በአዲስ አበባ ውስጥ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እየተፈጸመ ነው ፤ ወደፊት በሁሉም ዘንድ እንደ ሚሆን ተስፋ እናደርጋለን ።

✶ ✶ ✶

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በአቶ እጅጉ ረታ አዘጋጅነት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ታሪክ የተጻፈውን ተመልክቸዋለሁ የድንግል ማርያምን ታሪክ ለሰው ልጅ የዋለችውንና አሁንም የምትውለውን ቸርነት ሁሉ ተከታትለው አቶ እጅጉ ረታም ሆነ ሌሎች የእመቤታችን ወዳ ጆች ለሕዝብ ቢቻል በየወሩ ባይቻ ልም እንደተመቻቸው ቢገልጡልንና ለዚህም ድርጅት ልናደርገው የሚገባ ርዳታ ቢኖር ቢገልጡልን እኔ ሳልሆን መሰሎቼን ይዤ የምተባበር መሆኔን በደስታ እገልጣለሁ ።

ሰሎሞን ዮሐንስ
በከፍተኛ ፲፰ ቀበሌ ፳፯
አ/አ

● አቶ ሰሎሞን ዮሐንስ ስለ መጽሔ ታችን ያቀረቡት አስተያየት መልካም ነው እጅግ እናመሰግናለን።ስለ እመቤ ታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አስደናቂ ታሪኮች ብዙ ጊዜ በተከ ታታይ ጽፈናል ለምሳሌ በትንሣኤ መጽሔት ከቁ- ፲፭—፳ ወጥቶአል ወደፊትም በይበልጥ እንጽፋለንና መጽሔቱን በማንበብ መረዳት ይቻ ላል ። ለድርጅቱ ልናደርገው የሚ ገባ ነገር ቢኖር ቢገልጡልን ስላሉት ለጊዜው የድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣና የትንሣኤ መጽሔት ደንበኛ በመሆን በሥራችን ሁሉ ቢተባበሩን ደስ ይለናል ። ስለማንኛውም መንፈሳዊ አስተያየት በሚከተለው የስልክ ቁጥር ይደውሉልን ፲፭-፷፮—፲፯ አ/አ

★ ★ ★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ በፊት የማክበር ሰላምታዬን አቀርባለሁ እስከ አሁን ድረስ በጋ ዜጣም ሆነ በመጽሔት ስለሚወጡት ጽሑፎች አመሰግናለሁ። ለወደፊቱም ከዚህ በበለጠ እንደምትሠሩ እምና ለሁ በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር ፲፯ ወ/ት ተስፋነሽ በጫማ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስለመግባት ጠይቃ የተ

ወደ ፳፩ው ገጽ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች

ባለፈው ጽሑፍ ሐዋርያው ቅዱስ እን ጳውሎስ በሮምም ሆነ በተሰሎንቄ እንዲሁም በየገጠሩና በየከተማው በሚገኙ በተረሱ ሕዝቦች መካከል እየተገኘ የመንፈስ ንቃት እንደሰጠና የክርስቶስንም ቃል እንዳስተማረ መጻፌ ይታወሳል ።

አሁን ደግሞ ወቅቱ የዘመን መለወጫ በመሆኑ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቁ በተረሱ ሕዝቦች መካከል እየተገኘ እንደአስተማረ እጽፋለሁ ።

መጥምቁ ዮሐንስ በአሪትና በወንጌል መሸጋገሪያ ዘመን የተገኘ ሐዋርያና መልካም ካህን ነበር ይህ ከሆነ ከሐዋርያና ከካህን ፤ የሚፈለገው ምንድነው ? ከወይን ዛፍ ጣፋጭ ወይን እንጂ ኮምጣጤ እንደማይፈለግ እያከራከርም በዚህ ምሳሌ ረገድ ከአንድ ካህን ወይም ከአንድ ሐዋርያ የሚፈለገው እውነተኛ ትምህርት ነው ።

በያመቱ የዘመን መለወጫን በዓል የምናከብርለት መጥምቁ ዮሐንስ በተረሱ ሕዝቦች መካከል እየተዘዋወረ እነሱን መስሎ ያስተምር ነበር ። ልብሱም የግመል ጠጉር ሲሆን መታጠቂያውም ጠፍር ፤ ምግቡም የበረሀ ጣዝማ ማር ነበር ። የሚያስተምረውም ትምህርት « ፪ ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል ፤ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ » ይል ነበር ፤ ሊጠመቁ ለመጡትም ቀራጮች «ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ አላቸው ጭፍሮችንም በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም በሀሰት አትከሰሱ ደመወዛችሁም ይበቃችኋል » እያለ በይሁዳ ምድረ በዳና በሌሎችም ገጠሮች እየተዘዋወረ የተረሱ ሕዝቦችን ያስተምርና ለመንግሥተ ሰማያት ያዘጋጅ ነበር ።



መጥምቁ ቅ/ ዮሐንስ ስለ እውነት በሄሮድስ ትእዛዝ አንገቱን ተቆረጠ ።

እሱ በነበረበትም ዘመን የኑሮ ደረጃ ያልተስተካከለ ስለነበር ጌቶች ከድሆች ጋር መኖር አይፈልጉም ነበር፤ ጌትነትንና ድህነትንም የተፈጥሮ አቋም አድርገው ብዙዎቹ ይገምቱ ነበር ። ሆኖም ሰው ከሠራ ፤ ከነቃና ከተማረ እኩል እንደሚሆንና አንዱ ከሌላው እንደማይበልጥ መንገዱን አዘጋጁ ፤ ጥርጊያውንም አቅኑ ተራራው ዝቅ ይበል ስርጉጥጉጡ ይስተካከል ጐድጓዳው ይሙላ ሲል ያስተማረበት ምክንያቱ ይህ ነው ።

ከገጠርም ወደ ከተማ ለማስተማር በገባ ጊዜ ጊዜውን የተከተለ ትምህርት ለተረሱ ሕዝቦች አስተማረ መልካም ምሳሌም እየሆነ ከመታየቱም ሌላ አድልዎ እንዳይኖር ፍትሕ እንዳ ይጎድል ያለአንዳች ፍርሃት መሠከረ።

እሱም በነበረበት ዘመን ጋብቻ ተመሰቃቅሎ ፤ መፋታት በዝቶ ፤ ምንዝርም በርክቶ ሴቶችም ተንቀውና ተዋርደው ነበር ፤ ከዚህም የተነሳ አንዲት ሴት በአንድ ወንድ አንድ ወንድም በአንዲት ሴት ጸንቶ እንዲኖር ደጋግሞ አስተማረ ።

ለዚህም መረጃ የሚሆነን በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲፬ ከቁ. ፫—፲፪ ያለውን ብንመለከት ሄሮድስ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት አግብቶ ነበር ስለዚህ ሄሮድስ የወንድምህን ሚስት ልታገባ አይገባህም ። ሲል መከረው እሱንም ብቻ ሳይሆን ትንሹም ትልቁም በአንዲት ሴት ፀንተው እንዲኖሩና ካሁን ቀደም በትርፍ የያዝዋቸውን እንዲያሰናብቱ ቃሉን ባደባባይ አስተላለፈ ።

ይህም ትምህርቱ በተረሱ ሕዝቦች መካከል ተወዳጅነትን አተረፈለት ሄሮድስም ይህንን ስለፈራ ዮሐንስ ሐሳቡን እንዲለውጥ ጠርቶ አስጠነቀቀው ዮሐንስ ግን ሹመት ሽልማት የማይፈልግ ፤ ክብር የማይሻ ድሀ ነው ብሎ የማይፈራ ፤ ታላቅነው ብሎ የማያፍር እውነተኛ ሐዋርያና ካህን ስለነበር ከአንድ ካህን የሚፈለገውን መንፈሳዊ ተግባር ከመፈጸም አሳቡን አልለወጠም ።

ሄሮድስም ምክሩን ስላልተቀበለው ዮሐንስ አሠረው በመጨረሻም ሄሮድስ የልደት በዓሉን በሚያከብርበት ጊዜ ዘፋኞችን ለማስደሰት የዮሐንስን አንገት አስቆረጠው ። የዮሐንስን ያህል ሐዋርያና ካህን ለልደት እንደሚሰጥ ስጦታ ተቆጥሮና የፈንጠዝያ ዕቃ ሆኖ ለዘፋኞች መደሰቻ እንዲሆን መሰጠቱ ያሳዝናል ፤ ምክንያቱም ከአንድ አስተዳዳሪ ይህን የመሰለ መጥፎ ተግባር አይጠበቅምና ነው ።

ዮሐንስ ግን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ታሠረ ፤ ስለ እውነትም በመመስከሩ ተንገላታ ፤ እስከ ጊዜ ሞቱም ድረስ ታማኝ ሆኖ በመገኘቱ የማያልፈውን አክሊል ተቀዳጀ ።

በዚህ ዓለም ሲኖር ለራሱ አልኖረም ግን ለኅብረተሰቡ ኖረ ቢሞትም ለእግዚአብሔር ነው የሞተው ለራሱ አልሞተም ። ከአንድ ሐዋርያና ከአንድ ካህን የሚፈለገው ይህ ነውና መጥምቁ ዮሐንስም ይህንን በመሥራቱ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ታስታውሰዋለች ።

የሚያስደንቀው ደግሞ ሽላሚውም ሆነ ተሸላሚዎቹ ከነሥራቸው ሲያልፉ የስጦታ ዕቃ የሆነው ዮሐንስ ግን ለምእመናን መንፈሳዊ ስጦታ ሆኖ መኖሩ ነው ። ለቤተ ክርስቲያንም እንደ ክብር እቃና እንደ መልካም መታሰቢያ ሆኖ መንፈሳዊ ቅርስነትን ይዞ በየጊዜው የሚገኙትን መንፈሳውያንን ጐብኝዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲጠራ ይኖራል።

በዚህ አኳኋን ዮሐንስ ቢሞትም ሥራው አልሞተም፤ ቢቀበርም ሥራው ከመቃብር በላይ ሕያው ሆኖ ይኖራል ፤ ከአንድ ሐዋርያም ከአንድ ካህንም የሚፈለገው መልካም ተግባር ይህ ነውና ።

በሌላም በኩል ደግሞ በአንዳንድ ካህናት ፍርሐት እንዳለ እንመለከታለን ፤ በሉቃስ ወንጌል ም/፲ ከቁ. ፳፱—፴፯ ያለውን ብናነብ በወንበዴዎች ተደብድቦ በመንገድ ላይ ወድቆ ያጣጥር የነበረውን ምስኪን ካህናቱ እያዩ ተራምደውት ከመሄድ በቀር አንዳችም ርህራሄ አላደረጉለትም ። ነገር ግን ከካህን የሚፈለገው ይህ አልነበረም ከካህን የሚፈለገው መሥዋዕትነትና መንፈሳዊ ድፍረት ፤ መርዳት ፤ ርህራሄ ማድረግም ነበር ፤ ምክንያቱም የሰላምና የአንድነት የፍቅርም ምልክት ሆኖ መገኘቱ ከካህን የሚፈለግ በመሆኑ ነው ።

እንግዲህ በዘመናችን እንዲህ ያሉ ካህናት ይፈለጋሉን የሚል ጥያቄ ይቀርብ ይሆናል ። የወደቀውን የማያነሱ ፤ በተረሱ ሕዝቦች መካከል እየተገኙ የማያነቁ ፤ የታመመውን የማይጠይቁ የተጣላውን የማያስታርቁ ፤ የእግዚአብሔርን ቃል በአደባባይ የማይመሠክሩ ፤ የወደቀውን ድሀ ተራምደውት የሚያልፉ ካህናትና ሐዋርያት በኅብረተሰቡ ዘንድ አይፈለጉም ።

ስለ እንዲህ ያሉትም ካህናት ነቢዩ ሆሴዕ « ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል አንተም እውቀትን ጠልተሀልና ለእኔ ካህን እንዳትሆነኝ ጠላሁህ» ብሏል ። ነቢዩ እንዳለው በዚህ ተግባር የሚመሩ ካህናት ምስኪኑን ደብድበው በመንገድ ከጣሉት ወንበዴዎች አይሻሉም ማለት ነው ።

ይህ ከሆነ በዘመናችንም ስለዕውነት የሚመሠክሩ በተረሱ ሕዝቦች መካከል እየተገኙ ሰላም ፤ እኩልነት ይኑር ሥራ ፈትነት ይቅር ፤ ሥራ ይስፋፋ ፤ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ይከበር መፋታት ይቅር ፤ እያሉ እንደ ዮሐንስ የሚያስተምሩ በዘመናችን ብርቱ ካህናት ይፈለጋሉ ሳያስተምሩ በካህን ስም መጠራት አይቻልምና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ ።





www.ethiopianorthodox.org

**የወጣቶች ዓምድ**

# የወንጂ ሸዋ ሃይማኖተ አበው መንፈሳዊ ማኅበር ዓመታዊ በዓሉን አከበረ

በወንጂ ሸዋ እመሸንኮር ኪዳነ ምሕረት የተቋቋመው ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅርንጫፍ ማኅበር የተመሠረተበትን ፩ኛ ዓመት ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፸፩ዓ.ም. በደመቀ ሁኔታ አክብሮ ውሏል ።

በዚሁ ዕለት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ፤ ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ የዚሁ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ዛሬ የልማት ኮሚሽን ዋና ጸሐፊና አቶ አዳም መላኩ የሃይማኖተ አበው ዋና ጸሐፊ የሞጆ የናዝሬትና የወንጂ ሃይማኖተ አበው ቅርንጫፍ ማኅበራት ተወካዮች እንዲሁም በርከት ያሉ ምእመናን እና ወጣቶች በበዓሉ ላይ ተገኝተዋል ።

ቀደም ሲል ማኅበሩ ባወጣው መርሐ ግብር መሠረት በዓሉ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. በዋዜማው ከ፰ ሰዓት ጀምሮ የተከበረ ሲሆን በዚሁ ዕለት ልዩ ልዩ መዝሙሮችን የማኅበሩ መዘምራን ከማሰማታቸውም ሌላ ስለ እግዚአብሔር ህላዌ የሚገልጥ ሰፋ ያለ መንፈሳዊ ትምህርት ከኢ. ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት በተላኩት መምህር በመሪጌታ ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ ቀርቧል በመጨረሻም ስለአብርሃም እንግዳ ተቀባይነትና ደግነት የሚ ገልጥ አጭር ድራማ በወጣቶቹ ቀርቦ ከታየ በኋላ የዕለቱ ዝግጅት አበቃና ወጣቶቹ በዚያው አደሩ ።

በማግሥቱ ሐምሌ ፰ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. እሑድ ከየማኅበሩ የተወከሉትና የበዓሉ አዘጋጅ ወጣቶች በእመሸንኮር ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ባስቀደሱበት ወቅት በዚያ ለተሰበሰ ቡት ምእመናን መንፈሳዊ መዝሙሮ ችን አሰምተዋል በዚሁ ወቅት ከኢ. ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋ ርያዊ ድርጅት የተላኩትም መምህር የወንጌል ትምህርት ሰጥተዋል ።

፭ ሰዓት ሲሆን ብፁዕነታቸው በዓ ሉን በጸሎት ከፍተው ፕሮግራሙ ቀጠለና መሪጌታ ግርማ አበበ በተከ ታታይ ሦስት መወድስ ቅኔዎች አበረ ከቱ ከዚያም መንፈሳውያን መዝ ሙሮች ተዘምረው ካበቃ በኋላ ወይ ዘሪት ፀሐይ የማነ የወንጂ ሸዋ ሃይ ማኖተ አበው ቅርንጫፍ ማኅበር ሊቀ መንበር ሰፋ ያለ ንግግር አድርጋለች።

የወንጂ ሸዋ ሃይማኖተ አበው የኢ. ትዮጵያ ተማሪዎች ቅርንጫፍ ማኅበር ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. በአባ ወልደ ኢየሱስና በወ/ት ፀሐይ ግምባር ቀደምትነት የተመሠረተ መሆኑን ገልጣ «ምንም እንኳን ማኅበሩ ገና ጨቅላ ሳለ አባ ወልደ ኢየሱስ ወደ ሶደሬ ቢቀየሩም «እግዚአብሔር የመሠረተውን ማን ያፈርሰዋል » እንደተባለው ወጣቶቹ ራሳቸውን በማ ጠናከርና ከወንጂ ሃይማኖተ አበው ማኅበር ወጣቶች ጋርም ተዋውቀን በነሱም አማካይነት ከየረርና ከረዩ አውራጃና ከዋናው ሃይማኖተ አበው አጠቃላይ ጽ/ቤት ጋር በመገናኘት የዋናው ቅርንጫፍ ማኅበር አባል በመሆን ለማንኛውም ቅርንጫፍ ማኅ በር የሚደረግለት የመጻሕፍትና የመ ሪያ ርዳታ ተደርጎልን ከቀድሞ ይልቅ አሁን በመጠናከር መንፈሳዊ ግዳጃችንን በመፈጸም ላይ እንገኛ ለን ብላለች ።

ወይዘሪት ፀሐይ በንግግርዋ እንደ ገለጠችው ማኅበሩ መሰብሰቢያ አዳ ራሽ ስላልነበረው በመጀመሪያ በወ ንጂ ሸዋ እመሸንኮር ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ በሜዳው ላይ ሲሰበሰቡ ቆይተው ዛሬ ያ ሁሉ አልፎ በመጠኑም ቢሆን በሕ ዝበ ክርስቲያኑ ገንዘብ በተሠራው የክርስትና ቤት ውስጥ የሚሰበሰቡ ሆነዋል ። በመምህር እጦትም ያለው ችግር ለሸዋና አካባቢው በተመደበው ሰብከተ ወንጌል ብርቱ ጥረት መቃለ ሉን ተናግራለች ። ቀጥላም ስለማኅበሩ ፕሮግራም ስትገልጥ «ባለፈው ዓመት በየሳምንቱ ቅዳሜ ከ፰—፲ ሰዓት ሰፋ ያለ ትምህርት ለወዛደሩና ለአካባቢው ሕዝብ ሲሰጥ ቆይቶ የበጋው ወራት የፋብሪካው የሥራ ጊዜ በመሆኑ ለጊዜው ተቋርጦ በክረምት ብቻ እንዲሆን ቢደረግም ፍላጐት ያላቸው ሁሉ ግን ባላቸው ትርፍ ጊዜ ከወጣቶቹ ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እየተከ ታተሉ ይገኛሉ» በማለት የሰበካ ጉባ ኤውንና የወላጅ ኮሚቴውን እንዲ ሁም ለማኅበሩ የሞራል ድጋፍና እስ ተዋጽኦ ያደረጉትን ሁሉ አመስግና ንግግሯን አጠቃላለች ።

ከዚያም ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ያላ ቸው ድርሻ በሚል ርእስ ተነሥተው ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተዋል ። በትም ህርታቸውም የቤተ ክርስቲያንን ትር ጉም ከተነተኑና ካስረዱ በኋላ መድኃ ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕፃንነቱ ጊዜ ጀምሮ ከቤተ መቅደስ ጋር የነበረ ውን ግንኙነት ገልጠዋል ፤ በዚህም መሠረት በተወለደ በ፵ ቀኑ ወደ ቤተ መቅደስ መወሰዱንና በ፲፪ ዓመቱ በቤተ መቅደስ ገብቶ ከመምህራኑ ጋር ይከራከርና ይጠይቅ እንደነበረ አስታውሰው በዚያ ጊዜ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም «ፈልገንህ አጣንህ» ብትለው ስምለን ፈለጋችሁኝ በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንደሚገባኝ አላ ወቃችሁምን? ብሎ እንደመለሰላት ካብራሩ በኋላ የዚያን ጊዜዋ ቤተ መቅ ደስ የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ስለሆነች ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቦታ እንዳላቸው እንገነዘባለን ሲሉ ተናግረዋል ።

«ከዚህም ሌላ» አሉ ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ክርስቶስ በሚያስተምርበት ወቅት የትምህርቱ ተካፋዮች ወጣ ቶችና ሽማግሌዎች ነበሩ እንዲያውም ሐዋርያት ሕፃናቱን ለመከልከል ቢሞ ክሩ ሕፃናትን ወደኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው በማለት ከማዘዙም በላይ በሆሳዕና ዕለት ወደቤተ መቅ ደስ በሚገባበት ጊዜ » ቤቴን የሸቃ ጮች ቤት አደረጋችሁት» እያለ አዋቂ ዎቹን በጅራፍ ሲያባርር ሕፃናቱ ግን ዘንባባ በመያዝ እያመሰገኑትና እያ ጀቡት ታይተዋል ። ታዲያ ይህ ሁሉ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ድርሻ የሚያስረዳ ነውና በዚህ ቦታ ያላችሁ የሰበካ ጉባኤ አባላት ይህን አውቃችሁ ወጣቶች ልጆቻችሁ በቤተ ክርስቲያናችሁ ቦታ እንዲኖራቸው በማድረጋችሁና በዝግጅታቸውም መተባበራችሁ የምትመሰገኑ ናችሁ ብለዋል ።

በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያን እኩ ልነትን የምትሰብክና ጭቆናን የምታ ወግዝ በመሆኗ ብዙ ካህናት ለሀገራ ቸው ዳር ድንበር ፤ ለነፃነታቸው ክብር ሲሉ ሕይወታቸውን ሰውተዋል ይህም ዛሬ ሳይሆን ቀደም ሲል ተያይዞ የመጣ በመሆኑ የነ አቡነ ጴጥሮስ ደም ምስ ክር ነው ። ነገር ግን ይህን የማያውቁ አንዳንድ ግለሰቦች በቤተ ክርስቲ ያን ላይ ያላቸው አስተሳሰብ የተዛባ እንዳይሆን ከታሪክ መማር አለባቸው ብለዋል ። ቀጥሎም ወጣቶች በመካከ ላቸው ሰርጎገቦች ገብተው እንዳይ በርዟቸው በመጠንቀቅ ንጹሑን የኦ ርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት በሥራ መተርጎም አለባቸው በማለት አስገን ዝበው ትምህርታቸውን ፈጽመዋል ።

በፕሮግራሙ ፍጻሜ ላይ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ባሰሙት መንፈሳዊ ንግግር «ያለኔ ምንም ማድረግ አትች ሉም » የሚለውን ቃለ ወንጌል አስታ ውሰው የምንሠራው ሥራ ሁሉ እን ዲቃናልን በመጀመሪያ የእንግዚአ ብሔርን ፈቃድ መጠየቅ አለብን በማለት እግዚአብሔር ያለና የነበረ ፤ ወደፊትም የሚኖር ኃያል አምላክ መሆኑን በምዕዳናቸው አስምተዋል ።

ብፁዕነታቸው «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» የሚ ለውን የጠቢቡን ሰሎሞንን ቃል በማ ብራራት «ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን ከፈራ ማንኛውንም ወንጀል አይፈጸ ምም ስለዚህ ሰው ሁሉ ፈጣሪውን እንዲፈራና ሕጉንም እንዲያከብር የቤተ ክርስቲያን ካህናት በርትተው ማስተማር አለባቸው በማለት አስ ገንዝበዋል ። ከዚህም ጋር ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን እያመጡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ማስተዋወቅ ያለባቸው መሆኑን በማ ስገንዘብ ለልጆቻችሁ ልብስና ጉርስ የምታስቡትን ያህል ስለሃይማኖታ ቸው እንዲያውቁና ለወላጆቻቸውና ለሀገራቸው ጠቃሚ ዜጎች እንዲሆኑ በክርስቲያናዊ ግብረ ገብነት መገ ንባት ያስፈልጋቸዋል ። ይህ የወላ ጆች ብቻ ሳይሆን የካህናትም ግዴታ ነው ብለዋል ። በመጨረሻም «ማን ኛውም ክርስቲያን በ፵ ቀን መጠመ ቅና በበዓል ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን መሔድ ስለማይበቃ ሁልጊዜ ቤተ ክርስቲያንን እያሰበ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መኖር አስፈላጊ ነው ። ይልቁንም ሥራ ምስክር ነውና እያን ዳንዳችን ተቀዋሚዎቻችንን በመ ልካም ሥራችን ማሳመን አለብን» ብለው ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ንግግ ራቸውን እንዳበቁ ጸሎተ ቡራኬ አድ ርገው የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

## ማሳሰቢያ

በየአብያተ ክርስቲያናቱ የደረሰውን የልብሰ ተክህኖ ችግር ለማቃለልና ለማስወገድ በሥራ ጥናትና ዕቅድ መመሪያ ተጠንቶ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተፈቅዶ ፤ ፩ኛ/በመናገሻ አውራጃ በዓለም ገና ወረዳ አስተዳደር ፤ በስበታ ቤተ ደናግል ጠባባት ገዳም ፪ኛ/በመንበረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት ግቢ የልብሰ ተክህኖ ማደራጃና ማከፋፈያ ከ፲፱፻፸ ዓ·ም ጀምሮ ተቋቁሞ ሥራው በጥሩ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ነው።

የተቋቋመበትም አላማ ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ የሚሆ ኑትን ንዋያተ ቅድሳት የቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ ጽ/ቤት እያዘጋጀ በልብሰ ተክህኖ በኩል ያለውን ችግር ለማቃለልና ምእ መናንንም በከፍተኛ ዋጋ ከነጋዴ ዎች ከመግዛት ለማዳን ነው ።

ስለዚህ የአምስት ልዑካን ልብሰ ተክህኖ ዋጋ ብር ፪፻ መሆኑን እየገለጽን ፈላጊዎች በጠቅ ላይ ቤተ ክህነት እየመጡ መግዛት የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን ።

«ኢትዮጵያ ትቅደም»

ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል

የዕቅድና ጥናት ኃላፊ

ስልክ 12-49-03

ፖ.ሣ.ቁ. 12-83





www.ethiopianorthodox.org

# እምነት ስትመዘን

የኑሮ ሁሉ መሠረትና ጣራ እምነት ናት ፤ እምነት በፍጥረት ሂደት ሩጫ ሕይወትን ትመራለች ። እምነት የጥልቅ ምሥጢር መሥዋዕት የተስፋም ፍጻሜ ናት ።

ሰው ከየቤቱ ወጥቶ ከሥራ በኋላ ወደየቤቱ የሚመለሰው በመንገድ ሁሉ የሚያዘግመው በእምነት ነው ። እምነት በኑሮአችን ከፍተኛውን ቦታ ይዛ የምትገኝና ያለ እሷ ፍጹም ለመኖር እንደማይቻል የዚህ ጽሑፍ አንባቢ ሁሉ ሕይወቱን መርምሮ ያላትን ውጤት ሊገነዘብና ሊያስተውለው ይችላል ። እምነት ፤ ተስፋና ፍቅር ጸንተው ይኖራሉ ። ከሁሉ የሚበልጠው ፍቅር እንኳ በእምነት ካልተመሠረተ እውነተኛ ፍቅር አይሆንም ።

በሥጋዊ ኑሮአችን እምነት ይህን ያህል ታላቅ ከሆነች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለንእምነትማ የቱን ያህል እጅግ ታላቅ ነው ፤ የያዝናት እምነት በክርስቶስ በኩልታላቅ ሀብት ሆና ሕይወት ታሰጣለች ። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ። ከእኔ በቀር ወደአብ የሚመጣ የለም » ዮሐ.፲፬፥፮ ያለን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነቱ ሥር ብቻተጠልለን ሕይወትን ለማግኘት እንደምንችል በቃሉ አረጋግጦልናል ።

እግዚአብሔርን አምነን ጽድቅና ኩነኔ መኖሩን ተረድተን ለእኛሲል የተሰቀለውን ጌታችን ኢየሱስንተቀብለን በሃይማኖት ክርስቲያን ተብለን በቤተ ክርስቲያን እቅፍ ተሰብስበናል ። በዚህምበእምነት የማይታየውን አይተናል ። ይህን የመጀመሪያ እምነታችንን አጽንተን ብንጥጠብቅ የክርስቶስተካፋዮች ሆነናልና ዕብ ፲፩፥፱—፫ ። እነሆም ክርስቶስን ለመምሰል ያለፉት ነቢያትና ሐዋርያት በእምነት ድል እንደነሱ እኛም ደግሞ አስፈላጊያችን ይሆናል ። የክርስትና ሕይወት ተፈትኖ ማለፍን የሚጠይቅ መከራና ችግር የመሳሰሉትን አቀበቶችና ቁልቁለቶች መውረድና መውጣት ያለበት ለመሆኑ የሚወደኝ መስቀሉን ተሸክሞ ዕለት ዕለት ይከተለኝ » ሉቃስ ፱፥፳፫ ብሎ ያስከተለን አምላካችን ክርስቶስ በሕያው ቃሉ መንገዱን መርቶናል ። እኛም ይህን ሁሉ ዳገትና ቁልቁለት ወጥተን ስንገኝ ያኔ ዓለምን እናሸንፋለን ። ለምሳሌ ያለፉት የእምነት ዐርበኞች ያደረጉት ድንቅ ሥራ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎልናል። እኛም በነገርሁሉ ያለንን ከእግዚአብሔር ፍቅር ማነስ ካልሆነ በቀር ሊያግደን የሚችልምንም ዓይነት ነገር አይኖርም ። ሐዋርያው ጳውሎስ «መዋረድንም አውቃለሁ ፤ መብዛትንም አውቃለሁ ፤ በእያንዳንዱ ነገርም ሁሉ መጥገብና መራብን መብዛትና መጉደልን ተምሬአለሁ ፤ ኃይልን በሚሰ ጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ » ፊል.፬፥፲፪ ሲል በክርስትና ሕይወቱ ያስመሰከረውን በእምነት ኃይል ልናደርገው የማንችል እንደሌለ ነግሮናል ። ጌታችንኢየሱስ« በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ። ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁና » ዮሐ.፲፮፥፴፫ ይህ የጌታ ቃል መከራ እንዳለብንና እርሱን ከታመን ደግሞ በድል እንደምንወጣ እንዲሁም ነፋስ ቢነፍስ ፤ ማዕበል ቢነሣ ፤ ጐርፍ ቢጐርፍ አለት በሆነው በክርስቶስ እምነት እግሮቻችንን ካቆምን እንደማንናወጥ በማቴ.፯፥፳፬—፳፯ በምሳሌ ተነግሮናል ። ዳዊት« ምድር ብትነዋወጥ ፤ ተራሮች ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም » ያመለከነው የድል አምላክ የማይረታ አሸናፊው ጌታ አምላካችን ክርስቶስ በመሆኑ ፍርሃት የእምነት ትጥቃችንን እንደማያስፈታን ለትምህርት ፤ ለእምነትና ለጽናት እንዲሆነንየሰማዕታት ገድል በመጽሐፍ ቅዱስ ይገኛልና ። ስለዚህ ማንነታችን የሚታወቀው በመከራ ጊዜ ባለን ቁርጠኛ የክርስቶስ እምነት ብቻነው ዝናም ባይመጣ ሁሉም ቤት ተብሎዋልና ኃይለኛ ክርስቲያን በመከራ ይለካል እምነታችንም በየጊዜውይመዘናል ።

መከራ ከእግዚአብሔር የሚለየን ሳይሆን ፤ በበለጠ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበንነው ። ልትቀበለውያለህን መከራ አትፍራ እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሀለሁና ። ራዕይ፪፥፲። ጌታችን ኢየሱስ መከራና ስደት የመዳናችን ምልክት እንጂ እምነትን የሚያስጥለን አለመሆኑን እንዲሁ በመከራ ተፈትኖ ማለፍ እንጂ መከራን ለመፍራት አላስተማረንም « እግዚአብሔር የኃይልናየ ፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና» ፪ ጢሞ. ፩፥፯ ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል » የሐዋ ፲፬፥፳፪ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ እያለ መከራ ከእግዚአብሔር የለየን ስንቶችነን ? በማር. ፲፬፥፶፩ እንደተጻፈ ርቃናችንን በክርስትና ነጠላ ሸፍነን ከቆየን በኋላ በመከራና በችግርጊዜ ይህን የክርስትና እምነት ነጣላችንንአውልቀን የሸሸን ስንቶች ነን ? ስንቶችስ ሽክላ ክርስቲያን ሆነን በቀላሉበነፋስ ኃይል ተፈረካክሰን ቁጣንበላያችን አከማችተናል ? ስንቶቻችንስ እንደ ይሁዳ በዲናር ፤ እንደ ኤሳው በመብል ክርስቶስን ለውጠናል ? ስንቶችስ በመንፈስ ጀምረን በሥጋ ፈጽመናል ፤ እውነተኛ ክርስቲያን እስከ መጨረሻው ይታገሳል እስከ መጨረሻም ተስፋ ያደርጋል ። ስለዚህ የላሉትን እጆች ፤ የሰለሉትን ጉልበቶች አናቅና ያነከሰውም እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ ለእግሮቻችን ቅን መንገድ እናድርግ ዕብ.፲፪፥፲፪ በእርሱየሚያምን አያፍርምና ።

የእያንዳንዳችን ታላቅነት የሚመዘነው በሥጋችን ክብደት አይደለም። ትዕግሥት ታላቁን ኃጢአት ጸጥ ያደርጋል ፤ በፈተና የመጽናታችን ኃይልና የእምነት መጠን እሱ ሚዛናችንና ማንነታችን ነው ሰዎች እግዚአብሔርን ሲከተሉ ብቻ አይተን ብንከተለው እነሱ በከዱበት ጊዜም ምናልባት እነሱን ተከትለን እንዳንከድ እንጠንቀቅ ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእያንዳንዳችን እንደሞት ለጽድቃችንም እንደተነሣ ግወቅ ለእያንዳንዱ እንደየሥራው እስጠኛለሁ ያለንን ቃል እናስተውል ። ሐዋ· ጳውሎስ ወንድሞች ሆይ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉ የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ ይለናል ዕብ ፫፥፲፪

እነ ሲድራቅ ፤ ሚሳቅና ፤ አብደናጎ ወደ እሳት ሲጣሉ «ሕያው አምላካችን ከዚህ ከእሳቱ ያድነናል ፤ ለምስልህ አንሰግድም» በሚል ታላቅ እምነት ጸኑ ። በተጣሉ ጊዜም እንኳንስ ሊቃጠሉ ይቅርና የእሳቱ ሽታ እንኳ ሳይነካቸው በድል በአምላካችን ኃይል ወጡ ። እዚህ ላይ እነሲድራቅ ወደ እሳቱ እቶን ባይጣሉ ኖሮ ከእሳት የሚያድንና የሚያወጣ አምላክ መኖሩ በምን ይታወቅ ነበር ። ዳንኤልስ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ባይጣልና ኃያል አምላክ ከአንበሶች አፍ ባያድነው አዳኝነቱ በምን ይረጋገጥነበር ።

ይህ ሁሉ መከራ የሚመጣው የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጥና አዳኝነቱን ለማሳየት መሆኑን እንረዳለን ። እኛስ እምነታችን ስትመዘን ምንዓይነት ሰዎች እንደሆን እንደ ጴጥሮስ በክህደት እንምል ፤ እንገዛት ይሆን ? እርግጥ ጴጥሮስ በንስሐ ተመልሰዋል። እኛም እንመለስ ዕድል ሊያጋጥመን ይሆናል ። ነገር ግን ማወቅ ያለብን ደግሞ ኤሳው ንስሐን በዕንባ ተግቶ ስላልፈለገ ለንስሐ ሥፍራ አላገኘም እንዲሁ ሥፍራ እንዳናጣ እናስብበት።

እየወደቀ የማይነሣ የለም ፤ ወድቆ የማይነሣ ዲያብሎስ እንጂ ሰው ሊባል አይችልም በክርስትና ሕይወታችን መውደቅ መነሣት ቢፈራረቁበት በጠበበው በር ለመግባት እንትጋ ።

አብርሃም ዘመድ አዝማዱን ትቶ ከትውልድ መንደሩ በእምነት ወጣ፤ ሙሴ ከፈርዖን ቤተ መንግሥት ተድላ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በምድረ በዳ መከራን ለመቀበል በእምነትወጣ እሥራኤላውያንም ባሕሩን በእምነት እንደደረቅ ምድር ተሻገሩት እምነት እጅግ በጣም ታላቅናት በእኛ ሕይወትስ እንዴት ናት ?

ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደው መንገድ ጠባብ ነው የሚባለው በሚጓዝው ሰው ብዛት ሳይሆን ብዙ መከራና አስቸጋሪ ሕይወትንም የሚጠቅስ በመሆኑ ነው ለዚህ የጽድቅ ጉዞ በፍጹም ትዕግሥት ክርስቶስን ከመከተል ሌላ አቋራጭና መወጣጫ የለውም ። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመልተን ለሚበልጠው ብድራት ለነፍሳችን ክብር ሥጋችን የክርስቶስን መስቀል እንዲከተል እናድርግ። የምናደንቃቸው ነቢያትና ሐዋርያት በዚሁ በኩል ያለፉ ናቸው የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ ተጽፎዋልና ። ደስታ የማይፈነቅለን ለመከራ የማንበረግግ ሆነን በክርስቶስ እምነት የመመካት ኃይል ይኑረን ።

ግርማ ኃይሉ





www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዓምድ

« ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን » (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## ምሥጢረ ሥላሴ

«እግዚአብሔር» የሚለው ስመ አምላክ አንድነትና ሦስትነት አለው። ነገር ግን አንዳንድ አማኞች የእግዚአብሔርን አንድነት አምነው ሲቀበሉ ሦስትነቱን ይክዳሉ ወይም መቀበል ይሳናቸዋል ።

ታዲያ የአንድነቱም ሆነ የሶስትነቱ ማስረጃ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ነው ። ለምሳሌ ከመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ (ዘፍጥ ፩፤ ፳፮)«ሰውን እንደምሳሌያችን በመልካችን እንፍጠር» በማለት ሦስትነቱን ያስረዳል ። በዘፍጥ ፫ ፤ ፳፪ «አዳም ከእኛ አንዳ አንዱ ሆነ» የሚል ቃል ይገኝል በዚሁ መጽሐፍ ፲፩፤፯ ላይም « ኑ እን ውረድና ቋንቋቸውን እንደባልቀው» በሚል አነጋገር የእግዚአብሔርን ሦስትነት ይከሥታል ።

ስለዚህ የእግዚአብሔር አንድነት ሳይዘነጋ ማለትም እግዚአብሔር በባሕርይ በሕልውና በአምላክነት አንድ ሲሆን በአካል በግብር ፤ በስም ሦስት ብሎ አምኖ መቀበል የእውነተኞች ክርስቲያኖች እምነት ነው ።

ታዲያ ይህ አባባል የሦስትነት ማስረጃ ሆኖ ሳለ እስከ ዘመነ ሥጋዌ በግልጥ አልታወቀም ነበር ለአይሁድ ሊቃውንትም እንቅቅልሽ ሆኖ ባቸው የእግዚአብሔርን አንድነት ተቀብለውት ሳለ ሦስቱነቱን ለማመን ተቸግረውበት ስለነበር በተነገረው ትንቢትና በተቆጠረው ሱባኤ የሰውን ዘር ሁሉ ከኃጢአት ባርነት ነፃ ለማውጣት ወደነርሱ የመጣውን መሢሕ (ክርስቶስን) ለመቀበል ያላመኑበት ምክንያት ይኸው ነው ።

በሌላ በኩል እግዚአብሔር አንድነቱን ብቻ ሳይሆን ሦስትነቱንም በምሳሌ ሲያስረዳ ለሙሴ የገለጠለትን ምሥጢር እንደሚከተለው እንመለከታለን ።

ይኸውም በሲና ተራራ ላይ በእሳት አምሳል ሲገለጥለት ነበልባል ከሐመልማል ሐመልማል ከነበልባል ተዋህዶ« እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያእቆብ አምላክ ነኝ »በማለት ተናግሮታል ታዲያ አምላክ የሚለው ስም ሦስት ጊዜ ተደጋግሞ መነገሩ ሦስትነትን ያመለክታል ከዚህም ጋር« እግዚአብሔር» የሚለው ቃል ሦስትነትን የማመልከት ጠባዩ እንደተጠበቀ፣ ሆኖ በእዚህ አባባል ላይ አንድነትን የሚያመለክት መሆኑ እሙን ነው። ዘፀ ፫፤ ፲፫—፲፯ ማ. ፳፪ ፤ ፴፪

በዚህ አንፃር ሶስትነትን ለማመልከት የሚረዱ ሌሎች ጥቅሶች አሉ ከዚህም የተነሳ ዳዊት በመዝሙሩ « የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን መላ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ፀኑ ሠራዊታቸውም በአፉ እስትንፋስ» ሲል የተናገረውን ሊቃውንት ፩/ ሳህሉ ለእግዚአብሔር ሲል እግዚአብሔር አብን ፪ / ቃለ እግዚአብሔር ሲል እግዚአብሔር ወልድን ፫/ እስትንፋሰ አፉሁ ሲል እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል ሲሉ አጽንተውታል መዝ ( ፴፪ ፤ ፭—፮ ) ነቢዩ ኢሳይያስም የእግዚአብሔር ክብር በተገለጠለት ጊዜ መላእክት « ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባዖት ፍጹም እያሉ ሲያመስግኑት የሰማው መዝሙር የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚገልጥ መሆኑን ሊቃውንት አምነውበታል ።

እግዚአብሔር ለወዳጁ ለአብርሃም በሦስት እንግዶች ሰዎች አምሳል በተገለጠለትም ጊዜ ሦስትነቱን አመልክቷል ። ዘፍ ፲፰ ይህንና ይህንም የመሳሰሉት የብሉይ ኪዳን ማስረጃ እስከ ክርስቶስ ሰው መሆን ድረስ የሦስትነትን ምስጢራቸውን በጉልህ ለመረዳት ይከብድ ነበር የእነዚህ ሁሉ ምስጢር ትርጉም ግልጥ ሊሆን የቻለው ክርስቶስ የሰውን ዘር ለማዳን አምላክ ወሰብእ ሆኖ ወደዚህ ዓለም ከመጣ ወዲህ እርሱ ያስተማረውን የአዲስ ኪዳን ትምህርት መሠረት በማድረግ ስለሆነ በተከታዩ ጥቅሶችን በአጭር ትንታኔ ካቀረብን በኋላ የሊቃውንቱን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶክትሪን) እንቀጥላለን ።

ቄስ መከብብ አጥናው



# ሊቃውንቶቻችን

## ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ መምህር ኤስድሮስ

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ ስልትና ምርምር እንዲሁም የዕውቀት በር የከፈቱለት መምህር ኤስድሮስ በትግራይ ክፍለ ሀገር በተምቤን አውራጃ ተወለዱ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በዕለተ ልደታቸው የዓይን ብርሃናቸው ተጓልቶላቸው የተወለዱት እኒህ ታላቅ ሊቅ ከተወለዱ ከሠላሳ ቀን በኋላበዚያንጊዜ በኢትዮጵያ የሕክምና ጥበብ ባልተገኘለት በፈንጣጣ በሽታ ሁለት ዓይናቸውን እንደታወሩ ይነገራል ።

### አራት ዓይናው ኤስድሮስ

መምህር ኤስድሮስ በሰው ልጅች ተፈጥሮ መጠን የሁለቱ ይቅርና የአንድ ዓይን ብርሃን እንኳን ሳይኖራቸው የአራቱ ጉባኤያት መምህር በመሆናቸው «አራት ዓይናው ኤስድሮስ » ተብለዋል ፤

ለአራቱ ጉባኤያት ሊቃውንት «አራት ዓይና የሚያሰኝ የሊቅነት ስም የተጀመረው ለሊቅነታቸውና ለተመራማሪነታቸው ወደር በሌለው በመምህር ኤስድሮስ መሆኑ ስለታወቀ ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔር «ዕውራንን ጥበበኞች ወይም ዓዋቂዎች ያደርጋቸዋል» ብሎ የተናገረው በሊቁ መፈጸሙን ያመለክታል ።

### ትምህርት ቤታቸው

በተወለዱ በአሥራ አንድ ዓመት ዕድሜያቸው «እባ ሐደራ» ወደ ተባለ ገዳም ገብተው በታላቸው ፊደል ቆጥረው ዳዊት ከደገሙ በኋላ በጠቅላላው ፀጥትወ ዜማን ከአቋቋም ጋር በሚገባ አድርገው አጠኑ ።

ከዚህም ቀጥሎ የሊቁ የአእምሮ ገጽታ በቅኔ በሐዲስና በብሉይ እንዲሁም በመጻሕፍተ ሊቃውንትና በመጻሕፍት መነኮሳት ትርጓሜ እየበራና እየፈካ በመታየቱ የመጸሕፍትን ንባባቸውንም ሆነ ትርጓሜያቸውን በማፍታታትና በማመሥጠር ረገድ የነበረው ተጠያቂነት ሙሉ በሙሉ ለመምህር ኤስድሮስ ስለተሰጠ በኢትዮጵያ ሊቃውንት ዘንድ ስማቸውም ሆነ ሞያቸው ሳይጠገብ ኖሯል ።

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ሁሉ የቅኔ ትምህርታቸውን ተቅዋም በሚገባ አድርገው ያጠናከሩትና ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ለማስተማር የተመረቁት በታላቂቱዋና በስመ ጥሩዋ አክሱም ጽዮን ደብር ነበር ።

### ጉባኤያቸው

መምህር ኤስድሮስ በዚህ በኩል ይጉድላቸዋል ወይም ይህ ቀርቶአቸዋል ሳይባሉ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተምረው ታላቁ አራት ዓይና ከሚያሰኘው የትምህርት ደረጃ ከደረሱ በኋላ ወጥቶ ወርዶ በማባዛት ፋንታ እንዲቷን መክሊት እንደቀበረው ሰነፍ አገልጋይ መሆንን ስለአልፈቀዱ እንደደቀ መዛሙርቶቻቸው ምርጫና ፍላጐት የቅኔና የትርጓሜ መጻሕፍት ጉባኤያቸውን በየረድፉ አስፋፍተው ያስተምሩ ነበር ።

ከዚህም የተነሳ ሊቅ እንዲሁም «አራት ዓይና» የሚያሰኙትን ስሞቻቸውን ለደቀመዛሙርቶቻቸው አውርሰዋል ። በትምህርት ጉባኤያቸውም ጊዜ ተማሪዎቻቸው ብቻ ሳይሆኑ የምሥጢርንና የትርጓሜ ስልቶችን በመጠየቅ በትክክል ለመረዳት ከየአውራጃው ከየገዳማቱና ከየአድባራቱ በእንግድነት እየመጡ በዙሪያቸው የሚታዩት ሊቃውንት ብዛት በቀላሉ የሚገመት አልነበረም ።

ሊቁ ኤስድሮስ በማንም ሰው ተጠይቀው በሚሰጡት አስተማማኝ መልስ ተደስቶ የጥያቄውን ይዘት አጧልቶ የማይመለስ እንዳልነበረ ታውቋል ።

ለመረጃም ያህል ከሮም የመጣ አንድ ከፍተኛ ሊቅ የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው ? ብሎ ቢጠይቃቸው ለጥያቄው የጥያቄ መልሳቸውን በማከታተል መብራት አብርተው እነሆ አሁን የዚህ መብራት ፊቱ ወዴት ነው ? ስለአሉት የዚህማ በአራቱ ማዕዘን ማለት በሁሉም ነው ስለአላቸው እንደዚህም ሁሉ የእግዚአብሔር ፊቱ



www.ethiopianorthodox.org

በሁሉ ዘንድ ነው ብለው አስረድተው ጠያቂው በመልሳቸው ተደንቆና አመስግኖ ተመልሷል ።

## በትምህርትና በምርምር ያበረከቱት አስተዋጽኦ

መምህር ኤስድሮስ ከቀድሞ ማለት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ተያይዞ እንደቆየው ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሩት የላይ ቤትን ትርጓሜ ሐዲሳት ነበር ፤ ሆኖም የላይ ቤቱ ትርጓሜ እጅግ የረዘመ የአተረጓጎምና የአወራረድ ስልት ያለው ስለነበረሊቁ ይህን ትርጓሜ ለማቀነባበርና ቀልጣፋ የሆነ ተወዳጅ ስልት ወደ ከፍተኛ የምርምር አቅጣጫ በግላቸው አመሩ ።

ለዚህም ተግባራዊ ውጤት ይረዳቸው ዘንድ የጣናን ደሴት ለጊዜያዊ ማረፊያና ለመጻሕፍት መመርመሪያ መረጡ ፤ ይህም ደሴት በፀጥታው ለምርምር ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ ሌላ የጥንታውያን ቅዱሳት መጻሕፍት ክምችት በብዛት የሚታይበት ስለሆነ ሊቁ በሁለቱም በኩል ስለጣና ደሴት ሁኔታ ተደስቱ በዚሁም ደሴት ቅዱሳት መጻሕፍትን አንድ በአንድ ሲመረምሩ በቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የተተረጐመ ትርጓሜ ሐዲሳት ስለአገኙ የተማሩትን የላይ ቤቱን ፤ እንዲሁም በምርምር ያጋጠማቸውን የታች ቤት ትርጓሜ በማዋሐድና የቅልጥፍናን ፈር በማስያዝ ቅንብራዊ ትርጓሜያቸውን በጽሑፍ አደራጅተው ደቀ መዛሙርቶቻቸውን የተሻሻለውን ትርጓሜ ሐዲሳት እንዲማሩላቸው ጠየቁዋቸው ።

## አንዳንዶቹ ደቀ መዛሙርተ ከመሻሻል አፈነገጡ

ሊቁ ያሻሻሉትን የሐዲሳትን ትርጓሜ ዝርዝር ሁኔታውንና ጥቅሙን በማስረዳት ተማሪዎቻቸው እንዲማሩላቸው ቢጠይቋቸው ብዙዎቹ ፈቃደኞች ሆነው ወዲያውኑ ጉባኤ ሲዘረጉ አንዳንዶቹ « እኛ ከመሰሰን በፊት የተወለድን ነን» (ንሕነሰ ኢተወለድነ እምዝሙት) በማለት የሊቁን የምርምር ሂደት እንደመሰሰን ቆጥረውት አንማርም ብለው ከጉባኤው ስለአፈነገጡ ከመንፈሳዊ ዕውቀት የተጣበበና ውሱን በሆነ አእምሮ ላይ ሆነው ቀርተዋል ። ከተማሪዎቻቸውም መካከል አንደኛው ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ ናቸው»

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሊቁ ኤስድሮስ ያሻሻሉት ትርጓሜ የታች ቤትተብሎ ሲጠራ አስቀድሞ የነበረው የላይ ቤት እንደተባለ ቀረ ፤ ሆኖም ብዙዎቹ ሊቃውንት የመምህር ኤስድሮስን ትርጓሜ ስለ ተቀበሉ እነሆ የታች ቤት ትርጓሜ ሐዲሳት በሰፊው ተናኝቶ ይገኛል ። ሲያያዝ ወርዶም ወልደ አብ ወልደ ሚካኤል በኋላም እነ መምህር አካለ ወልድና በዜና ማርቆስ ገዳም የነበሩት መምህር ወልደ ሚካኤል እንዲሁም አቡነ ይስሐቅና የመሳሰሉት ሁሉ የመምህር ኤስድሮስን የሐዲስ ትርጓሜ ተከትለዋል ።

ታላቁ ሊቅ መምህር አካለ ወልድ በመጀመሪያ ያጠኑት የላይ ቤትን ትርጓሜ ስለነበረ የመምህር ኤስድሮስን የታች ቤት ትርጓሜ ቀደም ብለው የተማሩት መምህር ወልደ ሚካኤል እንዳጋጣሚ የመምህር አካለ ወልድ የጉባኤ ቦታ ወደነበረው ወደቦሩ ሜዳ ስለሔዱ መምህር አካለ ወልድ ከሊቁ ኤስድሮስ የወረደውን የላይ ቤት ትርጓሜ ለማጥናት መምህር ወልደ ሚካኤልን እንደጠየቁና እንዳጠኑ ይነገራል ። በሊቅነታቸው የታወቁትም መምህር ደስታ በኋላ አቡነ አብርሃም የመምህር ኤስድሮስን የታች ቤት ትርጓሜ ከመምህር ወልደ ሚካኤል ተምረው ብዙዎች ደቀ መዛሙርቶችን አስተምረዋል ። ከነዚሁም መካከል መምህር ሰይፉ በቀጥታ ከጉባኤያቸው ሲማሩ መምህር ቀጸላ ዛሬ አቡነ እንድርያስም በሚገባ አድርገው ከመምህር ሰይፉ አጥንተዋል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የመምህር ኤስድሮስን የሊቅነት ደረጃ ሲያስረዱ በሐዲሳት እንዲሁም በውዳሴ ማርያም ትርጉም መካከል መምህር ኤስድሮስ እንዲህ እንዲህ ብለው ተርጉመውታል እያሉ ይጠቅሱአቸዋል ።

ይልቁንም መምህር ኤስድሮስ ለቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ ውለታ አላቸው በግራኝ ወረራ ምክንያት አብያተ ክርስቲያናት ከተቃጠሉ ፤ መጻሕፍት ከተቆነፃፀሉ በኋላ የመጻሕፍትን ንባባቸውንም ሆነ ትርጓሜያቸውን አቃንተው ለመጻፍና ለማስተማር ብርቱ ጥረት አድርገዋል ።

መምህር ኤስድሮስ ይህን ሁሉ አገልግሎት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሠርተው አልፈዋል ፤ ታሪካቸው ግን እነሆ ሕያው ሆኖ ይኖራል ።

ሊቁ የተወለዱበትና ያስተማሩዋቸው ሊቃውንት ስም ፤ እንዲሁም የዕረፍት ጊዜያቸው ባለመሙዋላቱ በዚህ ጽሑፍ ለጊዜው ባይገለጽም ወደፊት በተከታታይ ለአንባብያን እንደምናቀርብ ተስፋ አለን ።

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ





# የ፲፰ ዓመት በሽተኛ

በዚህ የጤና ዓምድ ዝግጅታችን የምናቀርበው በፎቶ ግራፋቸው ስለ ምንመለከታቸው ስለ አቶ ጌታቸው ደስአለኝ ይሆናል ። አቶ ጌታቸው ደስ አለኝ ከ፲፰ ዓመት ተኩል ጀምረው አሁንም በማንም መፍትሔው ሊገኝለት በማይችል የበሽታ ቁራኛ ላይ ሆነው በተለይም ከ፯ ዓመት ተኩል ወዲህ ደግሞ ከአልጋቸው ሳይነሱ በሥቃይ ላይ ይገኛሉ ። ስለዚህ በሽታ መነሻና ያደረጉአቸውንም መከላከያዎች እንዲያስረዱን ወደአሉበት ድረስ ሔደን በማነጋገር የሰጡንን መግለጫ በጤና ዓምድ ዝግጅታችን ለአንባቢዎች አቅርበናል ።



በጠንነታቸው ጊዜ አቶ ጌታቸው ደሳለኝ እኒህ ናቸው ።

አቶ ጌታቸው በሽታው ሲጀምራቸው ምን ያህል ጊዜ እንደሆናቸው በመጀመሪያ ጠይቀናቸው ነበር ። እርሳቸውም ሲመልሱ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ ም ከጥር ወር ጀምሮ ነው ሲሉ መልሰውልናል ። አሁን ፲፰ ዓመት ተኩል ማለት ነው ። በሽታው ሲጀምራቸው ያሳያቸውን ምልክትና ሁኔታ እንደሚከተለው አብራርተዋል ። በመጀመሪያ መሐል ራሴ ላይ ትንሽ ቁስል ሆኖ ወጣ ከዚያ በጣም ያሳክከኝጀመር እዚያው ወጥቶ አልቀረም በ፫ ወር ውስጥ መላው ራሴን አዳረሰው ፤ከዚያም ዝም ብዬ አካለሁ፤ በ፲፱፻፶፱ በሽታው በያዛቸው በሦስተኛው ዓመት ማለት ነው ሰውነቴ እያፈከፈከ ፤እየደማ ፤ እንደ ድንች እየተላጠ እየተቀረደደና እያሰቃየኝ መታየት ጀመረ፤ በበሽታው ሰውነቶቼ ሁሉ መታዘዝ አቃታቸው ፤ ቢቸግረኝ በቅባት እያለሰለስኩ እሞክር ነበር ። ግን ምንም ለውጥ አላገኘሁም ።

በዚሁ በሽታ እንደተያዙ ያደረጉአቸው መከላከያዎች ምንና ምን እንደሆኑም ሲያስረዱ ገና እንደጀመረኝ ልዩ ልዩ ሕክምናዎችን አድርጌአለሁ በሕክምና ብቻ ፲፪ ዓመት ሞክሬአለሁ ፤ ሐኪሞች ስለዚህ በሽታ ሲናገሩ አስቸጋሪ እንደሆነ ለማስታገስ እንጂ ለማዳን እንደማይቻልም ነግረውኛል ። በሽታው በሐኪሞች አጠራር እፕሶርያሲስ (በቆዳ ላይ እየወጣና እያሠቃየ ጤና የሚያሳጣ) ማለት ነው በሽታው ለተመልካች ቀላል ይመስላል ፤ ለተያዘው ግን እጅግ ከባድና ሙሉ ጤንነትን የሚነሳና የሚያሠቃይ ነው ። ስለዚህም ሐኪሞች በጣም ይረዱኝ ነበር ፤ እኔንም ለመዳን ሳይሆን ከሥቃይ እንኳ እንዲያስታግስልኝ ይረድሃል ለሚባሉት መድኃኒቶች ብዙ ሺህ ብር አውጥቻለሁ ።

ከሕክምና ሌላም በጸበል ፤ በልዩ ልዩ የሀገር ውስጥ መድኃኒቶችና የባዕድ አምልኮ እንኳ ሳይቀረኝ ብዙ ለፍቻለሁ ፤ በዚሁ ጊዜ ውስጥ ግን በ፷ ዓ. ም. መጨረሻ ሰዎች በተለያዩ የባዕድ ማምለኪያዎች ሄደውልኝ ነበር፤ እንደምድንም ከዚያው ተነግሮኝእኔም ዋጋቸው ውድ የሆኑ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ልሰጥ ሥዕለት አድርጌ ነበር ። እንደአጋጣሚም የእግዚአብሔር ፈቃድ ከነሱ ሀሳብ ጋር ተገናኘና ለጊዜው መጠነኛ ፈውስ አገኘሁ ። የሚያሳክከኝም ገላዬ ቀስ በቀስ ተወገደ፤ ሥቃዩም እየቀነሰ መጣ ፤ ከአልጋዬም ተነሣሁ ። ወደ ዕለት ተግባሬም ተሰማራሁ የተሳልኩትንም በየቦታው ማዳረስ ጀመርኩ ፤ ድኛለሁ በማለትም ወደአንደኛው ሰው ደጅ መሄድ ቀጠልኩ ። እግዚአብሔር በመንግሥቱ ያስቀመጠልኝን ድርሻ ሊነፍገኝ ስላልፈለገ እንደገና በታላቅ ሁኔታ ሕመሙ ከሦስት ወር በኋላ ብሶ መጣ ፤ ለካስ በፊትም ያዳነኝ እርሱ ሊፈትነኝ እንጂ ጠንቋይ ዛር አልነበረም ። ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሬ ሥቃዩን ለብቼ አገኘሁ ። በዚህም የእግዚአብሔርን ሥራ ለማድነቅና የሚፈውሰኝ እርሱ መሆኑን ተምሬአለሁ ። ከዚህ ሁሉ ልዩ ልዩ ሙከራዎች በኋላ በ፷፰ ዓ. ም. ማናቸውም ያድናሉ ወይም ያስታግሳሉ የተባሉ መድኃኒቶችን እርግፍ አድርጌ ትቼ ለእግዚአብሔር ራሴን ብተው ፈውስ እንደማገኝ በማመን ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ ሰውነቴን አሳልፌሰጠሁ ይላሉ ። ከላይ በሙሉ ጤንነታቸው ጊዜ የተመለከትናቸው አቶ ጌታቸው በበሽታው ውስጥ እያሉ ይህን ይመስላሉ ፤ ስምንቱን ዓመቶች ለበሽታው መከላከያ በመፈለግ አልጋ ሳልይዝ ነበርኩ ፤ከ፯ ዓመት ተኩል በኋላ ግን። በአልጋ ቁራኛ ሥቃዩን እቀበላለሁ የበሽታው ዓይነት ማሳከክ ስለሆነ ከማከክ የተነሣ ጣቴም ጐብጧል ፤ መንጋጋዬም በደንብ መከፈት አይችልም ፤ እግሮቼ እንደሚገባቸው አይሠሩም ፤ ሥሮቼና ጅማቶቼ ሁሉ በዚሁ በሽታ ጠንቅ ተለክፈዋል ፤ ከሰ



www.ethiopianorthodox.org

ውነቴ እየተፈቀፈቀ የሚረግፈው በትንሹ ከ፲፭ ጆንያ በላይ እየተጠራቀመ ተቀብሯል ።

ከሕክምናና ከልዩ ልዩ መድኃኒቶች በኋላ ራሴን ለእግዚአብሔር ካስረከብኩበት ከሦስተኛው ዓመት ወዲህ በእግዚአብሔር ቸርነት ቁጭ ማለት



በሕመማቸው ጊዜ ዳግማዊ ኢዮብ እየተባሉ የሚጠሩት አቶ ጌታቸው ደሳለኝ ፤

ችያለሁ ፤ እግዚአብሔርም ከእኔ ጋር ስለሆነ መከራውን በትዕግሥት እንድችለው አድርጎ ምንም እንኳ ሕመሜ አሁንም ቢያሠቃየኝ የነበረብኝ ትልቁ የመንፈስ ጭንቀቴ ተወግዶልኛል ። ደግሞም ለኑሮዬ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች እኔ ሳይኖረኝ እያዘጋጀ ይሰጠኛል ። አምላኬን አምኛለሁና ሁልጊዜ ደስተኛ ነኝ ይላሉ አቶ ጌታቸው በዚህ ሕመም አሁንም እየተሠቃዩ ።

በጤንነት ጉድለት የሚሰማቸውን እንደሆነም ጠይቀናቸው ነበር ፤ በበሽታው አሁንም ብሠቃይም ለእግዚአብሔር ራሴን በማስረከቤ ሕመሜን ሁሉ አስረስቶኛል ፤ መቼ እድናለሁ የሚለውንም የእኔን ሐሳብ ትቼ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን በማለት በመዳኔ ወይም ባለመዳኔ ሳላተኩር አለሁ ። ሆኖም በዚህ ለእኔ ፤ ወይም ለሌሎች ፈውስ የማይገኝለት በሚመስል በሽታ ብታመም እንኳ ፤ ሁሉን የሚችለው አምላኬ እንደሚፈውሰኝ በተስፋ እጠባበቃለሁ ። በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር እንደሆነ በእምነት አውቄአለሁ ። በዚህ በሽታ ውስጥ ፰ ዓመት ለመዳን የተሯሯጥኩበትን ጊዜ ሳሰላስል አሁን በመከራ ያለሁበትን ኑሮ እመርጣለሁ በእርምጥ ሆኜ እይቸዋለሁና ይላሉ አሁንም በዚሁ በሽታ የሚሠቃዩት አቶ ጌታቸው ። በመጨረሻም ለአንባብያን የሚያስተላልፉት መልእክት እንዳላቸው ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ ከዕብራውያን ም/፲፪ ፤ ፩—፲፩ ያለውን ከቅዱስ መጽሐፍ እንዲያነቡ ከገለጹ በኋላ የራሳቸውን አስተያየት ሲጨምሩ ከእንግዲህ ወዲህ ቆምኩም ፤ ታመምኩም ፤ ኖርኩም ሞትኩም ለክርስቶስ ነኝ እግዚአብሔርን አጥቼ በጤንነትና በደስታ ከምኖር እርሱን አምኜ በዚህ መከራ መኖርን እመርጣለሁ ፤ የሚያድንና የሚፈውስ እግዚአብሔር ነው ፤ ሁሉን እንደፈቃድህ ማለት ጠቃሚ ነው ። አምላካችንን አምኖ እርሱ ብቻውን ለሆነው መስገድ ቢፈቅድ በተአምራት ይፈውሰኛል ። ባይፈቅድም ምድራዊ ሕይወቴ በዚህ ሕመም ቢጐሳቆልም ከቅድስናው እንድካፈል ተስፋ በማድረግ ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ያወርሰኛል ብዬ በእምነት ላይ እገኛለሁ ።

ከዚህ በላይ የተገለጸው አቶ ጌታቸው ወደአሉበት ድረስ ሄደን ስለበሽታቸው ለጠየቅናቸው ጥያቄ የሰጡን መልስና የእርሳቸው መልእክት ነው ።

አሁን ደግሞ ወደራሳችን ዘወር ብንል አለን በምንለው ጤንነታችን ላይ ለአንድ ቀን የሚውልብንን በሽታ እንዴት ነው የምንሠቃይበትና የምንመረርበት ? እንኳን በዚህ ዓይነት በሽታ ከ፲፭ ዓመት በላይ ያለዕረፍት መሠቃየት ይቅርና የዚህ ዓይነቱን በሽታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኢዮብን ታሪክ እናንብብ ። ኢዮብ ሰውነቱ ሁሉ በቁስል በሽታ እንደተመታና እንደተሠቃየበት ብናነብ የአቶ ጌታቸውንም የበሽታ ሁኔታ መመልከት እንችላለን ። ስለዚህም የአቶ ጌታቸውን የበሽታ ሁኔታና ስለበሽታው በማማረር ሳይሆን በምስጋና መቀበላቸውን ያስተዋሉ ሰዎች ዳግማዊ ኢዮብ ይሏቸዋል ። ስለአቶ ጌታቸው በይበልጥ ለመረዳት ቢያስፈልግ ወደ አሉበት ድረስ ሄዶ ማረጋገጥ ይቻላል የዚህ ዓምድ አዘጋጅ በይበልጥ የተደነቀበት ቢኖር በዚህ ሥቃይ በሽታ ውስጥ እያሉ እግዚአብሔርን የሚያመልኩና የሚያመሰግኑ የተሰጣቸውንም በሽታ ያለማጉረምረም የተቀበሉ መሆናቸውን ነው ፤ እኛስ ጤናችን ከቁጥጥር ውጪ በሆነ በሽታ ቢያዝ እንዴት እንቀበለዋለን ?

ለአቶ ጌታቸው በዚህ አጋጣሚ የምናሳስባቸው እግዚአብሔርን በማመን ወደተለያዩ ጸበሎች በመሔድ ለሕመማቸው ፈውስ እንዲያገኙ ነው ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና አንድ ቀን ይፈውስዎታል ።

ወ/ት ንብረት አበበ



# ዜና ሀገረ ስብከት

## አዲሱ የኢትዮ ኦ· ተ· ቤ. ክርስቲያን የሲኖዶስ ሕግና ደንብ ሊሻሻል ነው

አዲስ አበባ ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ባለፈው ሐምሌ ወር ፲—፲፮ ፲፱፻፸፮ዓ/ም አስቸኳይ ስብሰባ አድርጎ ቤተ ክርስቲያንን ስለሚመለከቱ አንዳንድ ጉዳዮች ውሳኔ ያስተላለፈ መሆኑን የሲኖ



ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የቅ/ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የከፋ ሀ/ ስብከት ጳጳስ ፤

ዶሱ ጊዜያዊ ዋና ጸሐፊ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ገለጡ። በዚህም መሠረት የተላለፉት ውሳኔዎች ፡—

፩ኛ/ በየካቲት ወር ፲፱፻፸፩ ዓ/ም/ የወጣው አዲሱ የሲኖዶስ ሕግናደንብ እንዲተችበት በመጽሔት ከወጣበኋላ

ሀ/ ቤተ ክርስቲያኒቱ በአሁኑ ይዞታዋ በመንፈሳዊ አገልግሎታቸው የምታምንባቸውን ሰዎች ሁሉ ስለማያቅፍ አንዳንድ አረፍተ ነገሮች እንዲሻሻሉ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ካህናትና መምህራን አስተያየታቸውን በጽሑፍ ስለአቀረቡ ፤

ለ/ በሕጉ ውስጥ አንዳንድ ቃል ከሀገሪቱ ሕግ ጋር እንዲዛመድ የቅዱስ ሲኖዶሱ አባላት ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግረውበት እንዲሻሻል ስለ ተስማሙ ፤

፩ኛ/ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ፤

፪ኛ/ ከጉባኤ ሊቃውንት ፤

፫ኛ/ ከመንፈሳውያን ድርጅቶች በሚመረጡ ሊቃውንት ተጠንቶናተሻሽሎ እንዲቀርብ ቅ/ሲኖዶሱ ወስኖአል ።

፪ኛ/ የኢትዮጵያ ኦ-ተ-ቤ/ ክርስቲያን ከልዩ ልዩ መንፈሳውያን ድርጅቶች በምታገኘው ርዳታ ገዳማትን ለመርዳት በታቀደው መሠረት ሀ/በወንዶችና በሴቶች ገዳማት ስንት መነኮሳትና መነኮሳይያት እንዳሉ፤ ለ/በየገዳማቱ አካባቢ ምን ዓይነት ልማት እንደሚያስፈልግ በየሀገረ ስብከቱ ጳጳስ ተጠንቶ እንዲቀርብ ውሳኔ አሳልፎአል ።

፫ኛ/ በኢትዮጵያ በአንዳንድ አህጉረ ስብከት የተቋቋመው የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ያወጣውን ደንብ ቅ/ሲኖዶሱ ተመልክቶ በፊርማ አጽድቆታል ።

፬ኛ/ የግብፅ ቤ/ክርስቲያን መሪዎች ስለደረሰባቸው ሥልጣን ያቀረቡትን ጥያቄ በመቃወም ጉዳዩን ለሚመለከተው ሥልጣናዊ አካል ለማስረዳት ከሲኖዶሱ አባላት አንድ የጐጃም ሀ/ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስና ቆሞስ መልአከ ኃይል ወ/ያሬድ ከሌሎች መልእክተኞች ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ ከመወሰኑም ጋር ስለሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ተወያይቶ በውሳኔ እንዳጸደቀ አዲሱ የቅዱስ ሲኖዶስ ጊዜያዊ ዋና ጸሐፊና የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ አስረድተዋል ።

## ኢሉባቦር

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ጳጳስ ዘኢሉባቦር ሀገረ ስብከታቸውን ተዘዋውረው በመጐብኘት ጠቅላላ የሥራ መመሪያ ሰጡ።





ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በጋምቤላ ብሔረ ሰቦች መካከል የሥራ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ፤

የሰበካ ጉባኤን ለማጠናከር ቀደም ሲል በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ከመጋቢት ፳ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም/ጀምሮ እስከ መጋቢት ፲፭ ቀን ፸፩ ዓ/ም/ድረስ በሥሬ አውራጃ በቡሬ ወረዳ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን በመጐብኘት ለየሰበካ ጉባኤው አጠናካሪ መመሪያ ሰጥተዋል ።

ብፁዕነታቸው በተለይም ተረስተውና ተንቀው በቆዩት በጋምቤላ ጭቁን ብሔረሰቦች መካከል በመገኘት «እምነት ከተግባር ጋር» በሚል ርእስ ጠቃሚ ምክር በመስጠትና ለወደፊት በየአስፈላጊው ምክንያት በመካከላቸ



www.ethiopianorthodox.org

ው እንደሚገኙ አጽናንተዋቸዋል ። በዚሁም ጊዜ ከመጋቢት ፲፰—፲፺ ፲፱፻፸፩ ዓ/ም/ በተደረገው ውይይት የአውራጃው የመንግሥት ሕዝባዊድር ጅት ተጠሪዎች እንደተገኙ ሪፖርቱን ያቀረቡት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ካህናት ቀሲስ ብርሃኑ መንገሻ ጨምረው ገል ጸዋል ።

ብፁዕነታቸው የጋምቤላን የሥራ ጉብኝት ከፈጸሙ በኋላ ወደመንበረ ጵጵስናቸው መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻ ፸፩ ዓ- ም- ተመልሰዋል ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ እንደገና ለሥ ራ በመነሳት መጋቢት ፳፺ ቀን ፲፱፻ ፸፩ ዓ- ም- ወደቡኖ አውራጃ በመሔ ድ ለተቀበሏቸው ምዕመናንና ካህናት ወጣቶችም ጭምር አባታዊ ምክራቸ ውን ከሰጡ በኋላ «ዛሬ ቤተ ክርስቲ ያን ራስዋን በራስዋ ትርዳ ሲባል ትር ጉሙ ቤተ ክርስቲያን የምዕመናን ምዕ መናንም የቤተ ክርስቲያን እንደመሆ ናችሁ መጠን እንደግል ንብረታችሁ በማሰብ ለቤተ ክርስቲያንዋ አስተዋ ጽኦ አድርጉ ማለት ነው ይህን ስናደ ርግ ከእኛ አልፈን ሌላውንም ለመር ዳት እንችላለን ብለዋል» በዕለቱ የበ ደሌ መድኃኔ ዓለምን ቤ/ክርስቲያን ለማሠራት በገንዘብ አስተዋጽኦበኩል ምሳሌነታቸውን አሳይተው ምዕመ ናን እጃቸውን እንዲዘረጉ አድርገ ዋል ።

ብፁዕነታቸው በዚህ ዓይነት በሶርና ገባ አውራጃ በመቱና አካባቢው በመ ዘዋወር ሰበካ ጉባኤ ባልተቋቋመበት እያቋቋሙ ፤ የተቋቋመው እንዲጠና ከር መምሪያ በመስጠት ከፍተኛ ሐዋ ርያዊ የሥራ ጉብኝት በማድረጋቸው ምዕመናንን አስደስተዋል ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ «ሒዱና አስ ተምሩ» የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ሚያዝያ ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ- ም- የቴፒና ጉደሬ ወረዳ ዎችን በመመልከት በቴፒ ቅዱስ ጊዮ ርጊስ የሰንበቴ አዳራሽ ውስጥ ለጠቅ ላላ ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት የ ሥራ መመሪያ ሰጥተዋል ። በተደረገ ውም ውይይት ለአንዳንድ ችግሮች ማስወገጃ አቅዋም ተወስዶአል ።

ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. በየኪ ወረዳ ዝንኪ ቀበሌ ለሚገኙ ምዕ መናንና ካህናት መመሪያ ሰጥተዋል ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ካደረጉት ጉብ ኝት በቴፒና በየኪ ወረዳዎች ከፍተኛ የሥራ ውጤቶች እንዲገኙ አድርገዋል ውጤቱም በተግባር እንደተገለጸ መረ ዳት አያዳግትም ።

አቶ ልንገር ቸኮል ገቢ መደረጉ፤ አን ደኛው የሥራ ይዞታቸው ውጤትነው።

ሌላው ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ- ም-በየኪ ወረዳ በመገኘት ሥልጣነክህ ነት ሰጥተዋል ፤

ሥልጣነ ክህነት ከተቀበሉት አድባራ ትም ፤

በቴፒ ጊዮርጊስ ለ፳ ዲያቆናት ፤

በቆሴ ቅ- ማርያም ለ፩ ዲያቆንና ፩ ቄስ ፤

በየኪ ሚካኤል ለ፪ ዲያቆናት ፤

በየኪ ቅ-ኪዳነ ምሕረት ለ፬ ዲያቆ ናት ፤



ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በቴፒ ወረዳ ተገኝተው ትምህርትና ገለጻ ሲያደርጉ ፤

ለምሳሌ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ-ም- የቴፒ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲ ያን በዘመናዊ አቅድ እንዲሠራ ምዕ መናን ቃል መግባታቸው ፤ የወንጌልን ትምህርት ለምዕመናን ለማዳረስ ይቻ ል ዘንድ ድምፅ ማጉያ እንዲገዛ ባደረ ጉት ቅስቀሳ የአሳቡ ደጋፊዎች በርካ ታ በመሆናቸው ወዲያውኑ ብፁዕነታ ቸው ለአስተዋጽኦ ምሳሌ ሆነው ሲቀ ድሙ ገንዘቡ ተዋጥቶ ብር ፩፻፴፫ በ በሚጢ ቅ- ገብርኤልለ፩ ቄስ ፤

በሻይ ሥላሴ ለ፩ ዲያቆን ፤

በፊዲ ኢየሱስ ለ፩ ዲያቆን ፤

በጠቅላላ ለ፪ ቀሳውስትና ለ፲፺ ዲያ ቆናት ሥልጣነ ክህነት እንደሰጡ በደ ረሰን ሪፖርት ለመረዳት ችለናል ።

ብፁዕነታቸው ከሚያዝያ ፲፰እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. የ፪ኛ ውን ዙር አከናውነው ካበቁ በኋላ ፤ በመጓጓዣ እጥረት የተነሳ ከግንቦት



፩—፬ ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. ድረስ እንደገና በጉደሬ ወረዳዎች ተዘዋውረው ምክ ርና መመሪያዎችን ሰጥተዋል ፤ ከዚህ በኋላ ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. ጅማ ከተማ ገብተዋል ፤ ከዚያም ወደ መንበረ ጵጵስናቸው እንደተመለሱ ቀሲስ ብርሃኑ መንገሻ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ በላኩት ሪፖርትለመ ረዳት ተችሏል ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በሶርና ገባ አውራጃ በሁሉሙ ወረዳ ተዘዋውረው ባስተማሩበት ወቅት በጅምር ላይየሚ ገኘው የገባ ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲ ያን ዘመናዊ አሠራር በቶሎ እንዲያ ልቅ ከፍተኛ መመሪያ ሰጥተው ዛሬ ሥራው በሰበካ ጉባኤ አባላትና በአ ሠሪ ኮሚቴ ትጋት እየተካሔደ ቢሆ ንም ሥራው እስከአለቀ ድረስ በየጊ ዜው ከቦታው እየተገኙ ለማጽናናትና የሥራውን እርምጃ ለመቆጣጠር ቃል ገብተዋል ።

የብፁዕ አቡነ ታዴዎስን የሥራ ይዘ ትና ሒደት በመመልከት ሌሎች አባ ቶች ለሥራ ቢሽቀዳደሙ የቤተ ክርስ ቲያን ዕድገት በአስቸኳይ በተግባር እንደሚታይ አንጠራጠርም ።

ከበለጠ አበበ ።

# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና

## ፓትርያርክ ኤልያስ አረፉ

ደማስቆ ፤ የአንጾኪያና የመላው ም ሥራቅ ፓትርያርክ ኤልያስ ፬ኛ ሰኔ ፲፬ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. በደማስቆ አር ፈዋል ። እርሳቸውም ከመስከረም ወር ፲፱፻፷ ዓ.ም. ጀምሮ በአንጾኪያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤ/ ክርስቲያን ርእሰ ቤ/ክር ስቲያን ሆነው ቆይተዋል። በአረቦችና በፖለስታይን ጉዳይ ታላቅ ሚና ተጫ ውተዋል ። በ፲፱፻፷፬ (እ. ኤ) በፓኪ ስታን የእስላሞች ኮንፍራንስ በተደረገ ጊዜ ክርስቲያን መሪ እርሳቸውብቻ ተገ ኝተው ነበር።ፓትርያርክ ኤልያስ ስለ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ተሐድሶ ከሚጥሩ መሪዎች አንዱ ነበሩ ሲል ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰር ቢስ ቁ ፲፺ ሰኔ ፳፰ ፲፱፻፸፱ (እ. ኤ.) ገለጠ ።

## ጳጳስ ሐዚም ፓትርያርክ ሆኑ

ደማስቆ ሶርያ ፤ ባለፈው ሰኔ ወር ፲፱፻፸፩ ዓ- ም- በሞቱት ፓትርያርክ ኤልያስ ፬ኛ ምትክ ጳጳስ ሐዚምሐምሌ ፪ ቀን ፲፱፻፸፱ (እ- ኤ) የአንጾኪያና የመላው ምሥራቅ ክፍል አግናጥዮስ ፬ኛ በሚል ስም ለፓትርያርክነትተመ ርጠዋል ። ፓትርያርክ አግናጥዮስ በ ፲፱፻፳ (እ- ኤ) በማርዳ ሶርያ ተወለዱ በቤይሩት በሚገኘው ኢንተርናሽናል ኮሌጅና የአሜሪካ ዩኒቨርስቲ ቤይሩት ባችለር ኦፍ አርት ዲግሪ(ቢ.ኤ) ተቀ ብለዋል ።

በ፲፱፻፵፱ ወደፈረንሣይ ተልከው በቅዱስ ሰርግዮስ ኮሌጅ ነገረ መለኮት አጥንተው በ፲፱፻፶፫ ዶክትሬት ተቀብ ለዋል ፤ በሊባኖስ የብሥራት ኮሌጅ ዲን ሆነው አገልግለዋል ፤ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ጳጳስ ሆኑ ፤ ዶክተር ፓትርያርክ አግናጥዮስ ስለነገረ መለኮትና ፍልስ ፍና ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ በ መስጠት ስመ ጥር ናቸው ። ፈረንሣ ይኛ ፤ እንግሊዝኛ ግሪክ መስኮብኛና አረብኛ በሚገባ ይናገራሉ ቅዱስነታ ቸው የመካከለኛው ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ከሶስቱ ፕሬ ዚደንቶች አንዱ ናቸው ።

ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቢስ ሐምሌ ፲፱፻፸፱ (እ. ኤ)

# ደብዳቤዎች

ከ፲፩ኛው ገጽ የዞረ

ሰጣት መልስ « በልማዳችን ክልክል ነው» የሚል ነበር ። በእኔ በኩል ልክ አይደለም።የቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው ተብሎ መሰጠት ነበረበት ምክንያቱም በዘጸአት ፫.፭ ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ ጫማህን አውልቅ ብሎታል፤ ታዲያ የጫማ ማውለቅ ሕግ በዚህ የተመሠረተ አይደለምን ?

ሽመልስ ኃይሌ

አዲስ አበባ

● አቶ ሽመልስ ያቀረቡትን ጥያቄ ተመልክተነዋል እርስዎ እንዳሉት ለሙሴ የተነገረው ቃል በጫማ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት እንደማይ ገባ ያመለክታል ፤ ይህም እንደ ሕግ ሆኖ በኢትዮጵያ ሲሠራበት ኑሮአል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በአንዳንድ የከተማ አብያተ ክርስቲያናት በጫማ መግባት ተጀምሮአል ፤ ለምን እንዲህ ይሆናል ? ለሚለው ጥያቄ የሚሰ ጠው መልስ የቤተ ክርስቲያኑ ወለል ከሲሚንቶ የተሠራ ስለሆነ በብርድ ከሚመጣው በሽታ ለመከላከል ነው የሚል ነው በመሠረቱ ወደ ቤተ ክርስ ቲያን ሲገባ ጫማ አውልቆ ሸማ ታጥቆ ወይም በአምሳለ ትእምርተ መስቀል ተላብሶ መግባት ተገቢ ነው፤ «ጫማ አውልቆ ሸማ ታጥቆ»ሲባልም በዓይን የሚታየውን የላይኛውን ብቻ አይደለም ። ከእግረ ልቡና ውስጣ ዊውን የተንኮል የቂምና የምቀኝነትን ጫማ አውጥቶ በፍጹም ትህትና በቅ ንነትና በንጽሕና መቅረብ ማለት እንደሆነ ሊቃውንት ያስተምራሉ ። ለሙሴም የተነገረው ቃል ምሥጢሩ ፍርሃትንና ጥርጥርን ከልቡናህ አርቅ ማለት እንደሆነ ሊቃውንት ያመሠ ጥራሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

## አዲሱ ፋሺን ለአዲሱ ዓመት ይደርስልኛል ?

እንዲት ወጣት አዲስ የመጣውን የልብስ ስፌት ፋሽን ለማሰፋት ጨርቅ ይዛ ወደ ሰፊ ዘንድ ሄደች ።

ሰፊውም ከለካላት በኋላ ለአዲሱ ዓመት ይደርስልኛል?ስትልጠየቀችው እርሱም ፋሽኑ ገና አዲስ ነውና ከሁለት ሳምንት በኋላ ባደርስልሽ ጥሩ ነው ። በማለት መልስ ሰጣት ።

እርሷም እንዴ ! ከሁለት ሳምንት በኋላ ? እስከዚያ ድረስማ ፋሽኑም ሆነ አዲሱ አመት ያልፋል አለችው።

ሰፊውም ሊሆን ይችል ይሆናል ! ነገር ግን ከአንቺ በፊት ልብስ ያመጡ ሌሎች አሉ ! ቢሆንም ከአንድ ሳምንት በኋላ ለማድረስ እሞክራለሁ ሲል መለሰላት። እርሷም ምነው የኔ ደንበኛ ከዛ ወዲህ ቢደርስልኝ ? እኔ እኮ አዲሱን ዓመት በአዲስ ፋሽን ለመታየት ፈልጌ ነው ። እባክህን አድርስልኝ ለአዲሱ ዓመት ከአዲስ ልብስ በስተቀር ሌላ ዝግጅት የለኝም አለችው ።

እርሱም እንግዲያውስ ልብሱን ውሰጅና እንደፈለግሽ አድርጊ አላት ።

በዚህ ጊዜ ወጣቷ ድንግጥ ብላ ሌላ ጥያቄ በመቀጠል ልብሱ ፋሽኑን (ሞዱን)ተከትሎ እንዲሰፋ እንጂ እንዲ በላሸብኝ አልፈልግም። ግን እንተፈቃድህ ቢሆን ልብሱን አሁኑኑ ለመስፋት ብትጀምርልኝ ምን አለበት ? አለችው ።

ሰፊውም ፈገግ ብሎ እንዲህ ሲል መለሰላት ልክነሽ አዲሱን ፋሽን ለመስፋት አሁኑኑ መጀመር ይገባል ምክንያቱም ከቆየ እንዳልሽው ፋሽኑም ሆነ አዲሱ ዓመት ያልፋል ብሏት ዕለቱኑ መስፋቱን ጀመረ ።

ይህች ወጣት በአዲሱ ዓመት አዲስ ፋሽን ልብስ ለመልበስ አሁኑኑ በጥድፊያ እንዲደርስላት ፈለገች ።

እዎ ሁሉም ሰው እንደ ወጣቷ አዲስ ዓመት ሲመጣ እንደ አቅሙና ችሎታው መሰናዶ ያደርጋል አዲስ ነገርም እንዲያገኝ ይፈልጋል ይኸውም አንዳንድ እናቶች በአዲሱ ዓመት ለእቴቴ ለቃልቻና ለመሳሰሉት መጥፎ ልምድ ለመገበርና ስብ ለማጤስ የሚዘጋጁ አሉ ። ይህም በክርስትና እምነታችንም ሆነ በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የተወገዘ ነው ። በተለይ ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምሮ አባሎቿ ከዚህ አይነቱ አምልኮ የነጹ እንዲሆኑ አጥብቃ ስታስተምር ቆይታለች አሁንም ታስተምራለች ። ይህም አይነቱ መሰናዶ በጽሑፋችን ውስጥ ከቁጥር አንጨምረውም ።

ግማሹ በአዲስ ዓመት አዲስ ልብስ ለመልበስ ሲዘጋጅ ሌላው በአዲስ ዓመት የሥራ እድገትና የደሞዝ ጭማሪ እንዲያገኝ ይመኛል ። እንደዚሁም ነጋዴው ካለፈው ዓመት የበለጠ ትርፍን ሲመኝ ገበሬውም የተሻለ ምርት እንዲያገኝ ይመኛል ሌላውም እንደዚሁ ።

ይሁን እንጂ ሰዎች በአዲስ ዓመት እንዲያደርጉ የሚያስፈልጋቸው ይህ ብቻ ነው?አይደለም።ልብ ብለን ካስተዋልን ወጣቷም ሆነች ሌሎቹ የዘነጉት አለ ። ይኸውም ለሥራም ሆነ ለእድገት ለሀገር ብልጽግናም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ጽናት ለሁሉም መርሆ የሚሆነው አዲስ መንፈስ ነው ከዚህም ጋር የሚያረጀውን ልብስ ብቻ ሳይሆን ለዘለዓለም የማያረጀውን እውነተኛውን የሃይማኖት ልብስ መልበስ ያስፈልጋል ። መጽሐፍ ቅዱስም አሮጌውን ሰውነት አስወግዱ በአእምሮአችሁም መንፈስ ለእውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰውነት ልበሱ ። ኤፌ. ፬፡፳፬

ሰዎች አላቂው ጨርቅ ለአዲስ ዓመት እንዲደርስላቸው «አሁኑኑ»ካል ተሰፋ ይላሉ ። የማያረጀው እውነተኛውን የብርሃን ክርስቶስ ልብስ ለመልበስ ግን ቀጠሮ በማራዘም ለሚመጣው ዓመት ! ለወዲያኛው ዓመት በማለትና ከዚያም አልፎ የእርጅናጊዜአቸውን የሚጠብቁ ጥቂቶች አይደሉም ።

ነገር ግን መዝሙረኛው ዳዊት « ጐልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው» ብሎ እንደ ተናገረው ሁሉ ቃሉን ለመጠበቅ ዕድሜ አይወስነውም አዲስ መንፈስና ቁርጥ ሃሳብ እንጂ ።

አንባብያን ለመሆኑ እናንተስ አዲሱን ዓመት በአዲስ ፋሽን ብቻ ወይንስ አዲሱን ዓመት በአዲስ መንፈስ ! አዲስ ሥራ ለመሥራት? ከየትኛው ወገን ናችሁ? በአዲሱ ዓመትስ በክርስትና ሕይወታችሁም ሆነ ለሃገራችሁ እድገት አሁኑኑ ለመሥራት ምን ያቀዳችሁት ሥራ አለ? ወይንስ ምክንያት በማብዛት ነገ ከነገ ወዲያ እያላችሁ ነው?

አንባብያን አስታውሱ ሁል ጊዜ ወጣቷ ከላይ እንደተናገረችው ሁሉ ጥሩውን ሥራ አረጋግጣችሁ ልትሠሩበት የምትችሉበት ጊዜ «አሁን» አሁኑኑ የተባለችው ሰዓት ብቻ መሆኗን አትዘንጉ አስታውሱ እያንዳንዱ ደቂቃና ሰዓት እያንዳንዱ ቀንና ወር የሕይወታችሁ ክፍል ስለሆነ ለነፍሳችሁም ሆነ ለሀገር እድገት የሚጠቅመውን ሥራ በፍላጐትና በደስታ «አሁን» አሁኑኑ በሚለው ጊዜ በመሥራት ተጠቀሙ ።

ታላቁ መጽሐፍ « እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ

ወደ ፳፰ኛው ገጽ ዞሯል



# አዛውንቶቻችን

መምህር ገ/ እግዚአብሔር ባደግ !

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ዜና መዋ ለጫ በሆነው በዚህ መድሔት ላይ የሚያውቃቸው እንዲያስታውሳቸው የማያውቃቸው በታሪካቸው እንዲ ተዋወቃቸው የስመ ጥሩውን ኢትዮጵያዊ ሊቅ መምህር ገ/ እግዚአብሔር ባደግ ዜና እንገልጻለን ።

መምህር ገብረ እግዚአብሔር ባደግ በሸዋ ክ/ ሀገር መንዝ ውስጥ ከአባታ



ከአዛውንቶቻችን አንዱ መምህር ገ/ እግዚአብሔር ባደግ ።

ቸው ከአዛዥ ባደግና ከእናታቸው ከወይዘሮ ሎሚታ የአማራ ሳይንት ሴት መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፰ዓ-ም ተወለዱ ።

ወላጅ አባትና እናታቸው በልጅነታቸው ስለሞቱባቸው ታላቅ ወንድማቸው መሸሻ ባደግ ሚጢኮራ ጊዮርጊስ ምንጃር ውስጥ ለመልከ ጼዴቅና ለአባ ሀብተ ሚካኤል በመስጠት ትምህርታቸውን በዚያ ሥፍራ ጀመሩ

መምህር ገ/ እግዚአብሔር ባደግ በልጅነታቸው ያሳደጓቸው የነበሩት ታላቅ ወንድማቸው መሸሻ ባደግ እጅግ ቅንና መንፈሳዊ ደግ ሰው ስለ ነበሩ በመንፈሳዊ ይዞታ ለመጠናከር ይህ አመቺ እንደሆነላቸው መምህር ገልጸውልናል ።

መምህር ገብረ እግዚአብሔር ባደግ በሚጢኮራ ጊዮርጊስ ዳዊት ደግመው ከጨረሱ በኋላ ቀሪው ዘመናቸውን ከዚህ በታች በተዘረዘረው ሥፍራ እየተዘዋወሩ ተምረዋል ።

፩ኛ/ ዳዊት ሚጢኮራ ጊዮርጊስ ደግመው እንደጨረሱ ዜማ በመማር እንጦጦ ኪዳነ ምሕረትና ራጉኤል መጥተው እየተማሩም ! እያገለገሉም በሊቀ ጠበብት መኰንን ቤት አክስታቸው ዘንድ ተቀምጠው ትምህርታቸውን ተከታተሉ ።

፪ኛ/ ድጓ በመማር ትግራይ በርከት ላስ ዘመን ከቆዩ በኋላ የደብረ ቢዘን ገዳም (ኤርትራ) ማኅበረ ሥላሴ ቋቲት ገዳም በጠቅላላው ሰሜናውያን የኢትዮጵያ ገዳማት የእግዚአብሔር ጸጋ የተመላባቸው በመሆኑ በድንግልና ለመኖር በመወሰን ከትግሬው መምህራቸው ከሊቀ ካህናት መርሻ ዘንድ ድጓ አስመስክረው በሰሜን በርከት ላሉት ዘመናት በመምህርነት አሳልፈው ሸዋ ተመልሰዋል ።

፫ኛ/ ከዜማ ትምህርት በኋላ የቀጪኔ መድኃኔ ዓለም ሲመሠረት ጀምሮ ፭ ዓመት ካገለገሉ በኋላ እንደገና በሚጢኮራ ጊዮርጊስ ከአቡነ ማቴዎስ እጅ ዲቁናን ተቀብለዋል ።

፬ኛ/ ቅኔ ለመማር በመጀመሪያ ብቸና ጐጃም ከመምህር ውብሸት ዘንድ ትምህርታቸውን ጀምረውበሚገባ ለመጨረስ ከታወቁት የዘመኑ የዋድላው የቅኔ መምህር ከነበሩት ከመምህር አወቀ ዘንድ ቅኔ ተቀኝተው ተመለሱ ።

፭ኛ/ ዜማ ለመማርና አስመስከረው ለመምጣት ከስመጥሩው የቤጌምድር ሊቅ መምህር ኃ/ ማርያም ዘንድ የዜማ ትምህርታቸውን ጨርሰው ቤተ ልሔም አስመስክረዋል ።

፮ኛ/ ጠላት ሀገሪቱን ከመውረሩ በፊት በ፲፱፻፳፯ ዓ/ ም/ በመናገሻ ማርያም የብሉይ መምህር የነበሩት መምህር ተክሌና ንቡረዕድ ክፍሌ መምህር ገብረ እግዚአብሔር ባደግን የመናገሻ መምህር እንዲሆኑ በመጠየቅ እስከዛሬ ድረስ ለ፴፬ ዓመታት የድጓና የዜማ መምህር በመሆን እያሌ ሊቃውንቶችን በመናገሻ ማርያም ገዳም አፍርተዋል ።

እናት ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናችን በዘመናት ሁሉ የአገራችንን ባህል ፣ ቅርስ፣ ታሪክ ፣ ቋንቋ በመጠበቅ እዚህ ከመድረሷም ሌላ ፣ ሊቃውንቶችን እንደመናገሻው መምህር ገ/ እግዚአብሔር ባደግ የ፴፬ ዓመታት የነፃ አገልግሎት የመምህርነት ዋጋ ባለማስጠየቋ አዲሱ ትውልድ ይህችን ባለውለተኛ ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቃት የዚህ ዓምድ አዘጋጅ ይጠይቃል ።

ያሬድ እስቻለው

## አዲሱ ፋሽን . . .

ከ፳፭ኛው ገጽ የዞረ

ጥሩት ይላል /ኢሳ ፶፭፡፮/ ደግሞም እነሆ የተወደደው ሰዓት አሁን ፣ ነው እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው ይላል ፪ ቆሮ ፮ ፡ ፪/ የዚህም ትምህርት «አሁን» የሚለውን ጊዜ እያንዳንዱ ሰው በሥራ እንዲያውለው የሚያመለክት ሲሆን በሳምንት በወር በዓመት ምን እንደምትሆኑ ስለማታውቁ በአለፈው ዓመት በአእምሮአችሁ የነበረውን መጥፎ አስተሳሰባችሁን ! ክፋት ! ተንኮል ! ምቀኝነት ስንፍናን ጥላቻን አውልቃችሁ ጣሉ በአዲሱም አመት«አሁን» አሁኑኑ በአዲስ መንፈስ በክርስቶስ ታደሱ ሃገራችሁንና ቤተ ክርስቲያናችሁንም በሥራ አድሱ የተሐድሶ ጊዜ አሁን ነውና ።

ወ/ት ብርሃን ተድላ



www.ethiopianorthodox.org

# የመስቀሉ ቃል

## የእግዚአብሔር ኃይል ነው

«ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ» የሚለው ቃል ለማያምኑት ሰዎች እንደ ሞኝነት ይቆጠራል ፤ ለምንድነው ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው ።
(፩ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፰)

### መስቀል መመኪያችን

እኔ ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት ፣ እኔም ለዓለም ከተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ የምመካበት ነገር የለኝም (ገላትያ ፮ ፡ ፲፬)

### መስቀል መድኃኒታችን

ሙሴ በበረሃ እባብን እንደ ሰቀለ ፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል ፤ ምክንያቱም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ ነው ። እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለወደደ አንድ ልጁን የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ እንጂ እንዲጠፋ አይደለም ። ይህንንም ያደረገው በልጁ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ እንጂ እንዲጠፋ አይደለም ። (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፬—፲፮ ።)

### መስቀል ሰላማችን

ለያይቶን የነበረውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰና አይሁዳውያንንና ዓረማውያንን አንድ ያደረገ ሰላማችን ክርስቶስ ነው ፤ ሰላምንም በማድረግ ከሁለቱ ሕዝቦች ከእርሱ ጋር የሚተባበር አንድ አዲስ ሕዝብ ለመፍጠር የሕግን ትእዛዞችና ደንቦች በሥጋው ሻረ ፤ በመስቀል ላይ በመሞትም ጠላትነትን አስወግዶ ሁለቱንም በአንድ አካል አድርጎ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቃቸው ፤ መጥቶም ለእናንተ ርቃችሁ ለነበራችሁና ቀርበው ለነበሩት ለእነርሱም የሰላምን ወንጌል ሰበከ ።
(ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፲፬—፲፯)

በእርሱም አማካይነት በሰማይም ሆነ በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ ከራሱ ጋር አስታረቀ በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙም ሰላምን አደረገ ። (ቆላ ፡ ፩ ፡ ፳ ።)



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ዩ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org